**አዋጅ ቁጥር170/2012 ዓ/ም**

**የተሻሻለ ው የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ያልተማከለ የወረዳ አካባቢ አስተዳደርን ለማጠናከር የወጣ አዋጅ**

የአካባቢ አስተዳደሮች የተሰጣቸውን ራስን በራስ የማስተዳደር ተግባር ተጠቅመው ህብረተሰቡን በማነቃነቅ የህዝቡን ተሳትፎና የውሳኔ ሰጪነት ሚናን በማጉልበት በሰው ኃይል፣በበጀትና በአሠራር ራሳቸውን በማጠናከር ለልማቱ መፋጠንና ለመልካም አስተዳደር ግንባታ ከፍተኛ ሚና እንዲጫወቱ ማድረግ ተገቢ በመሆኑ፤

በክልሉ ውስጥ የተቋቋሙት ቀበሌዎች በግልጽ በህግ ማዕቀፍ ውስጥ እንዲካተቱና ከዚህ በፊት የአከባቢውን ባህልና ወግ የሚያመላክት ስያሜ ያልነበራቸውን ወረዳዎችና ቀበሌዎች የስም ለውጥ ማድረግና ተጨማሪ ቀበሌዎችን ማቋቋም አስፈላጊ ሁኖ በመገኘቱ፤

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት በተሻሻለው የክልሉ ህገ መንግሥት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3 .1 ሥር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል፡፡

**አንቀጽ 1**

**አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ የተሻሻለው “የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ያልተማከለ የአካባቢ አስተዳደርን ለማጠናከር የወጣ አዋጅ ቁጥር---------/2012 ዓ/ም” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 2**

**ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ፡-

1. “ህገ-መንግስት” ማለት የተሻሻለው የ1995 ዓ/ም የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ህገ-መንግስት ነው፤
2. “ክልል ምክር ቤት” ማለት የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ምክር ቤት ነው፤
3. “መስተዳድር ምክር ቤት” ማለት የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት መስተዳድር ምክር ቤት ወይም ካቢኔ ማለት ነው፤

4. "የአካባቢ አስተዳደር" ማለት እንደአግባብነቱ ራሳቸውን ችለው እንዲተዳደሩ በፌደራሉና በክልሉ ህገ-መንግስት ስልጣን የተሰጣቸውና በአከባቢው መራጭ ህዝብ የተመረጡ የህግ አውጪ፣ የአስፈፃሚና የዳኝነት ስልጣን ያላቸው እንዲሁም የራሳቸውን ገቢ የመሰብሰብ ስልጣን ያላቸው የአስተዳደር አካላት ናቸው፤

5. "የወረዳ አስተዳደር" ማለት በፌደራሉና በክልሉ ህገ-መንግስት መሰረት ራሱን ችሎ የሚተዳደር ህግ-አውጪ፣ ህግ-አስፈፃሚና የዳኝነት ስልጣን ያለው የአካባቢ አስተዳደር ነው፤

6. "ምክር ቤት" ማለት በአካባቢው መራጭ ህዝብ የተመረጠ የአካባቢው አስተዳደር የህግ-አውጪ አካል ነው፤

7. "የወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት" ማለት በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ውስጥ በተቋቋመበት ወረዳ ከፍተኛ የህግ አስፈፃሚ አካል ወይም ካቢኔ ነው፤

8. "አስተዳዳሪ" ማለት እንዳግባብነቱ የአካባቢ አስተዳደሮች ከፍተኛ የስራ አስፈፃሚን የሚመራ ዋና አስተዳዳሪ ማለት ነው፤

9. "አስፈፃሚ መስሪያ ቤት ሃላፊ" ማለት በዋና አስተዳዳሪው የሚመረጥና እንደአግባብነቱ ሹመቱ በምክር ቤቱ ፀድቆ የአካባቢ አስተዳደሩን የአስፈፃሚ መስሪያ ቤት የሚመራ ኃላፊ ማለት ነው፤

10. "ያልተማከለ አስተዳደር" ማለት ከክልሉ መንግስት በህግ ለአካባቢ አስተዳደሮች የተሰጠ ስልጣንና ተግባር ነው፤

11. "የህግ ሰውነት" ማለት ራሱን በራሱ የማስተዳደር ስልጣን ያለው፣በህግ ተለይቶ የተሰጠውን ተግባራት የሚያከናውን በቀጣይነት መውረስና ማውረስ የሚችል፣ በህግ የታወቀ ማህተም ያለው፣በስሙ መክሰስ ወይም መከሰስ የሚችል የአካባቢ አስተዳደር ነው፤

12. "ቀበሌ" ማለት በወረዳ አስተዳደር ስር የተቋቋመና በውክልና የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር የሚያከናውን የወረዳ አስተዳደር የበታች አካል ነው፡፡

## አንቀጽ 3

## የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ አዋጅ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት በከተሞች አስተዳደር አዋጅ መሰረት ራሳቸውን ችለው ከሚተዳደሩ ከተሞች ውጭ በተሻሻለው የክልሉ ህገ-መንግስት ወይም በዚህ አዋጅ በተቋቋሙ ወይም በሚቋቋሙ የአካባቢ አስተዳደሮች ላይ እንደአስፈላጊነቱ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

## አንቀጽ 4

## መርሆዎች

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የፌደራሉንና የክልሉን ህግጋተ-መንግስት መሰረት በማድረግ የአከባቢ አስተዳደሮችን ለማጠናከር የሚከተሉትን ያልተማከለ አስተዳደር መርሆዎችን ይከተላል፡-

1. የአካባቢ አስተዳደሮች ዓላማቸውን ወይም ተግባርና ሃላፊነታቸውን በብቃትና ውጤታማ በሆነ መንገድ መፈጸም እንዲችሉ በቂ ስልጣንና ሐብት እንዲኖራቸው ማድረግ፤
2. የተጣለባቸውን ተግባርና ሃላፊነት በአግባቡ እንዲወጡ የሚያስችላቸው ሐብት የመሰብሰብና ስራ ላይ የማዋል ስልጣን እንዲኖራችው ማድረግ፤
3. በክልሉ ውስጥ ተግባሩን መወጣት የሚያስችል ቀልጣፋና ብቃት ያለው የአካባቢ አስተዳደር መዋቅር እንዲኖር ማድረግ፤
4. የአካባቢ አስተዳደሮች ተግባራቸውን በዲሞክራሲያዊ አግባብ፣ በግልፀኝነት፣በተጠያቂነትና አሳታፊ በሆነ መንገድ እንዲፈፅሙ የአቅም ግንባታ መስጠት፤
5. የአካባቢ አስተዳደሮች በአካባቢያቸው በልማት የመሪነት ሚና በመጫወት ለአገሪቱ ልማት የበኩላቸውን ሚና እንዲጫወቱ ማስቻል፤
6. የአካባቢ አስተዳደሮች የጋራ ጥቅማቸውን መሰረት በማድረግ የትብብር ስርዓታቸውን መገንባት፤
7. የአካባቢ አስተዳደሮች አካባቢያቸውን ለማልማት ለሚያወጡት ዕቅድና አፈፃፀማቸው አመቺ ሁኔታ መፍጠርና ድጋፍ መስጠት፤

8. ለአካባቢ አስተዳደሮችና ለተሰጣቸው ተግባርና ሃላፊነት ጠንካራ ህጋዊና ተቋማዊ መሰረት እንዲኖራቸው ማድረግ፤

9. የአካባቢ አስተዳደሮች አካባቢያቸውን በመንከባከብና የተፈጥሮ ሐብታቸውን በመጠበቅረገድ የመሪነት ሚና እንዲጫወቱ ማስቻል፤

10. በልማት ወደ ኋላ የቀሩ አካባቢዎች ያልተማከለ አስተዳደርን ለመተግበር የሚያደርጓቸውን ጥረቶች ለማገዝ የተለየ ትኩረት መስጠት፤

11. የአካባቢ አስተዳደሮችን ለማልማት በተለይም መሰረተ-ልማትን ለመዘርጋት በሚደረገው ጥረት መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ሲቪል ማህበረሰብና የግል ባለሃብቶችን ተሳትፎ ማበረታታት፤

12. የአካባቢ አሰተዳደሮች ተግባርና ሃላፊነታቸውን ሲወጡ ዲሞክራሲየዊ መርሆዎችን በመከተል የአካባቢውን ህዝብ በተለይም ሴቶችንና ትኩረት ያላገኙ የህብረተሰብ ክፍሎችን አቅማቸውን ማጎልበትና ማብቃት፤

13. ያልተማከለ አሰተዳደር ለውጦች ቀጣይነት እንዲኖራቸው የማያቋርጥ ጥረት ማድረግ፡፡

## አንቀጽ 5

## ዓላማዎች

ይህ አዋጅ እና ይዘቱ ያልተማከለ አስተዳደርን ለመወሰን የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

1. በክልሉ መንግስት ስር ያሉ የአካባቢ አስተዳደሮችን ይወስናል፤
2. በአካባቢ አስተዳደሮች ያልተማከለ ተግባርን፣ ስልጣንን፣ ሃላፊነትንና የሚሰጡአቸውን አገልግሎቶች ሙሉ በሙሉ ተፈፃሚነት እንዲኖራቸው ማድረግ፤
3. መልካም አስተዳደርን ለማጎልበትና ዲሞክራሲን ለማጠናከር፡-

   ሀ) አገልግሎቶችንና ውሳኔዎችን ወደሚመለከታቸው ህዝብ ተደራሽ በማድረግ አካባቢያዊ ቁጥጥርንና ተጠያቂነትን ለማጠናከር፤

   ለ) በልማት ዕቅዶችና በበጀት እንዲሁም በውሳኔ አሰጣጥ የአሳታፊነት ስርዓቶችን መዘረጋትና ማሳደግ፤

ሐ) የአካባቢ አስተዳደሮችን የውሳኔ አሰጣጥና አጠቃላይ ስራዎች ግልፀኝነት እንዲኖራቸው ማድረግ እና፤

መ) የካባቢ አስተዳደር ሃላፊዎች እና አገልግሎት ሰጪ አካላትን አገልግሎት ለሚሰጡት ህዝብ ቀጥተኛ ተጠያቂነት እንዲኖራቸው በማድረግ ፈጣን ምላሽ በመስጠት አገልግሎታቸውን እንዲያሻሽሉ ማድረግ፡፡

4. የህዝቡን የስልጣን ባለቤትነት ለማረጋገጥ፡-

ሀ) ህብረተሰቡ መብቱንና ግዴታውን በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና በፖለቲካዊ ጉዳዮች ድርሻውን እንዲወጣ በማበረታታትና በማስቻል በአካባቢ አስተዳደሮች ውስጥ ንቁ ተሳትፎ እንዲኖረው ማድረግ፤

ለ) የህብረተሰቡን ተሳትፎ በአካባቢያዊ አስተዳደር ውስጥ በማሳደግ ህዝቡ መብትና ግዴታውን በማህበራዊ፣በኢኮኖሚያዊና በፖለቲካዊ ጉዳዮች እንዲወጣ ማድረግ፤

ሐ) የአካባቢው ህብረተሰብ በአካባቢው የአገልግሎት አሰጣጥ ላይ የመቆጣጠርና የማስተዳደር ሃላፊነት እንዳለበት ማስተዋወቅ እና፤

መ) ሕብረተ-ሰቡ በአካባቢ አስተዳደር ተቋማት ላይ ከፍ ያለ የባለቤትነት ስሜት እንዲኖረው ማድረግ፡፡

5. ልማትን፣ እኩልነትንና የኑሮ ደረጃን ለማሳደግ፡-

ሀ) ለአካባቢው ኢኮኖሚያዊ እድገትና ብልፅግና ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር፤

ለ) በክልሎች በአካባቢዎችና በግለሰቦች መካከል ያለውን ያልተመጣጠነ ዕድገት መቀነስ፤

ሐ) በአካባቢው አስተዳደሮች ቀልጣፋና ውጤታማ የሆኑ ህዝባዊ አገልግሎቶችን በመስጠትና የልማትና አገልግሎት ሰጪ አካላትን ስራዎች ማቀናጀት፡፡

## ክፍል ሁለት

## የአካባቢ አስተዳደር ሥርዓት፣ መዋቅርና አመሰራረት

### አንቀጽ 6

### የአካባቢ አስተዳደር አጠቃላይ መዋቅር

የአካባቢ አስተዳደር የመዋቅር ስርዓት በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት እየተወሰነ በክልሉ ምክር ቤት ይፀድቃል፡፡

## አንቀጽ 7

## የአስተዳደር እርከኖች

የክልሉ የገጠር አካባቢ አስተዳደር እርከኖች የሚከተሉት ናቸው፡-

1. በህግ ተለይቶ ስልጣን የተሰጣቸው የብሄረሰብ አስተዳደር እርከን፤
2. በህግ ተለይቶ ስልጣን የተሰጣቸው የወረዳ የአካባቢ አስተዳደሮች፤
3. በወረዳ ምክር ቤት በተሰጠ የአስተዳደር ውክልና የተዋቀረ የቀበሌ አስተዳደር፡፡

## አንቀጽ 8

## የወረዳ አስተዳደር ሕጋዊ ሰውነት

ሁሉም የወረዳ አስተዳደሮች የማይቋረጥ የመውረስና የማውረስ መብት ያላቸው፣ በሕግ የታወቀ ማህተም ያላቸውና በስማቸው መክሰስና መከሰስ የሚችሉ ሕጋዊ ሰውነት ያላቸው አስተዳደሮች ናቸው፡፡

## አንቀጽ 9

## በሥራ ላይ የሚገኙ የወረዳ አስተዳደሮች

1. አሁን በሥራ ላይ ያሉና በዚህ አዋጅ እውቅና የተሰጣቸው የወረዳ አስተዳደር አካባቢዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

ሀ) አሶሳ ወረዳ
ለ) ባምባሲ ወረዳ
ሐ) ሆሞሻ ወረዳ
መ) መንጌ ወረዳ
ሠ) ሸርቆሌ ወረዳ
ረ) ኩርሙክ ወረዳ
ሰ) ቡልዲግሉ ወረዳ
ሸ) ማኦ እና ኮሞ ልዩ ወረዳ
ቀ) ማንድራ ወረዳ
በ) ዳንጉር ወረዳ
ተ) ጉባ ወረዳ
ቸ) ድባጤ ወረዳ
ኀ) ቡለን ወረዳ
ነ) ወምበራ ወረዳ
ኘ) ፓዌ ወረዳ
አ) ካማሽ ወረዳ
ከ) ዳምቤ ወረዳ
ኸ) ሰዳል ወረዳ
ወ) ምኙጋ ወረዳ
ዐ) ዛይ ወረዳ
ዘ) ኡንድሉ ወረዳ

2. በሥራ ላይ ያሉና በዚህ አዋጅ በአዲስ እውቅና የተሰጣቸው በወረዳ አስተዳደር ስር የሚገኙ ቀበሌዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

ሀ) በአሶሳ ወረዳ ስር

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አሀንሻ | 22 | ኮመሽጋ | 43 | አምባ 7 | 64 | መገሌ 29 |
| 2 | ገንገን | 23 | ጋምቤላ | 44 | አምባ 8 | 65 | መገሌ 30 |
| 3 | አጎሌ | 24 | ሩባለገዳ | 45 | አምባ 9 | 66 | መገሌ 31 |
| 4 | አሉቦ | 25 | ቡልድግሉ | 46 | አምባ 10 | 67 | መገሌ 32 |
| 5 | ቁሽመንገል | 26 | አፈሲዝም | 47 | አምባ 11 | 68 | መገሌ 33 |
| 6 | ዜዜ አዱርኑኑ | 27 | ያምባሲዝም | 48 | አምባ 12 | 69 | መገሌ 34 |
| 7 | አጎሻ | 28 | አፈ መገሌ | 49 | አምባ 13 | 70 | መገሌ 35 |
| 8 | ጉምባ | 29 | አባንቴ | 50 | አምባ 14 | 71 | መገሌ 36 |
| 9 | አቁዳ ቱመት | 30 | አብራሞ | 51 | አምባ 15 | 72 | መገሌ 37 |
| 10 | ኡራ | 31 | ሸርቆሌ ኢንጂ | 52 | አምባ 17 | 73 | መገሌ 38 |
| 11 | ሩባዩ | 32 | ሸርቆሌ አሆፌንዱ | 53 | ሆሃ 18 | 74 | መገሌ 39 |
| 12 | ባሮ | 33 | ቁሽመጋኒ | 54 | ሰልጋ 19 | 75 | ኡዳባ |
| 13 | ማናጌ ሰልጋ | 34 | ቡድሩ | 55 | ሰልጋ 20 | 76 | ጎልፃሃ |
| 14 | አፌደሆንሾ | 35 | ፉፉር | 56 | ሰልጋ 21 | 77 | ፍልደሩ |
| 15 | ቤልሚሊ | 36 | ቡልዳድኔ | 57 | ሰልጋ 22 | 78 | አጤጦ ሰልጋ |
| 16 | ፀንፀሀሎ | 37 | አምባ 1 | 58 | ሰልጋ 23 | 79 | ጋምቢሺሪ |
| 17 | ባሻ ቡዳ | 38 | አምባ 2 | 59 | ሰልጋ 24 | 80 | ጠረፈ ዳር |
| 18 | ዳቡስ አጠምባቆ | 39 | አምባ 3 | 60 | ኮሞሽጋ 25 | 81 | ታሳ ቤልጉንዲ |
| 19 | ሙጉፉዴ | 40 | አምባ 4 | 61 | ኮሞሺጋ 26 | 82 | ቁቆ |
| 20 | ኢንዢሸደሪያ | 41 | አምባ 5 | 62 | ኮሞሽጋ 27 | | |
| 21 | አጤጦ ኦንጎላሉ | 42 | አምባ 6 | 63 | ኮሞሺጋ 28 | | |

ለ) በባምባሲ ወረዳ ስር

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ባምባሲ 01 | 12 | አፉ ጋናሮ | 23 | መንደር 45 | 34 | ነባር ቀሽማንዶ |
| 2 | ባምባሲ 02 | 13 | ቡዳ ሰልጋ | 24 | መንደር 46 | 35 | ቀሽማንዶ ቁ.2/3 |
| 3 | ወምባ | 14 | ኢዳ ዳቡስ | 25 | መንደር 47 | 36 | ቀሽማንዶ ቁ.4/5 |
| 4 | ዳቡስ | 15 | ቦሽማ ቀረክክ | 26 | መንደር 48 | 37 | ሲሳ ቁ.1/2 |
| 5 | ሶንካ | 16 | ሸዮ በርጎሸ | 27 | መንደር 49 | 38 | ቦሽማ ማእከል 2 |
| 6 | ሾቦራ | 17 | ሙፃ ሲርና | 28 | መንደር 50 | 39 | ጎልማ |
| 7 | ጃማፃ | 18 | መንደር 40 | 29 | መንደር 51 | 40 | ሙፃ ሹዋራ |
| 8 | ኤሽን አልመተማ | 19 | መንደር 41 | 30 | መንደር 52 | 41 | ሰላማ ዳቡስ |
| 9 | ኤሽን አልከሻፍ | 20 | መንደር 42 | 31 | መንደር 53 | 42 | በርጎሸ |
| 10 | አፉ ቡልደሮ | 21 | መንደር 43 | 32 | መንደር 55 | 43 | ሸንክላ |
| 11 | አፉ ፊረቤናሬ | 22 | መንደር 44 | 33 | አምባ 16 | 44 | አየንዱ |

ሐ) ሆሞሻ ወረዳ ስር

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ቱመት | 5 | ጅማ | 9 | ዱንጋ አሩሜላ | 13 | ጉሙ አቡሹ |
| 2 | አልገልዓ | 6 | ሸርቆሌ | 10 | ፆሬ አልመተማ | 14 | ሞሎ መገሌ |
| 3 | ዳሬ ሰላም | 7 | ሹላ | 11 | አቀንዶ | 15 | አልፋሽር |
| 4 | አሹራ | 8 | ባማዶን | 12 | ዳረሰጊያ | | |

መ) ኩርሙክ ወረዳ ስር

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሆርአዘሃብ | 6 | ዱል ሸታሎ | 11 | አጉቤላ | 16 | ቤልጅብላ |
| 2 | በሸር | 7 | አቀንድዩ | 12 | ፋማጸሬ | 17 | አሙንዙቤኒ |
| 3 | ኩርሙክ | 8 | ሳሊማ | 13 | አባዲ | 18 | ኦግንዱ |
| 4 | ዱል ሆዴ | 9 | ሁሸርጉማ | 14 | ደላሼ | 19 | ቡልዲግሉ |
| 5 | አቤ ቤልኡሙ | 10 | አሸሽሬ | 15 | አደንገዝ | | |

ሠ) በመንጌ ወረዳ ስር

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ከሻፍ | 6 | ቀድዩ | 11 | ቱመት ጀበረና | 16 | ቱመት መንገዱል |
| 2 | ሸጎል | 7 | አቦራ | 12 | ፋጸቆ | 17 | ባኔ ሸታሎ |
| 3 | ቤልሙጎህ | 8 | ማሎ | 13 | ቤልዶሱ | 18 | አልፋሽር |
| 4 | ቱመት ሙኳር | 9 | ጊዘን አልመተማ | 24 | አበጀንቡ አሹመን | 19 | ሸንዲ |
| 5 | ኦፕ መገሌ | 10 | ቱመት በሪያ | 15 | ፈርዶስ | | |

ረ) በኡንዱሉ ወረዳ ስር

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሲኖር | 4 | ኡንዱሉ ኡርያ | 7 | ከተማ | 10 | አሆነ መንጋ |
| 2 | ሳላማ | 5 | ፉንዱዱ | 8 | ቤላ ፊዳ | 11 | ቤልምሊ |
| 3 | ኡንዱሉ | 6 | ሸጋ ደማዚን | 9 | አልአሀመር | | |

ሰ) በሸርቆሌ ወረዳ ስር

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሀልሞ ቤቤ | 6 | ሂሊታጀር ፋሻሊ | 11 | ፉዱርሴ ፋርቤጉ | 16 | አባሌኝንጻ |
| 2 | ሸ/ቤ/ቴ/ጎ | 7 | ኦቤ ኡቤ ኢሸ ፋቤጉ | 12 | ገ/ምጽምጽናሬ | 17 | ቆለሆ |
| 3 | ኦቤ ፉርቤጎ | 8 | ቱመት ኡቤ | 13 | ሆምቤ ሹዴ | 18 | አቤኔሪ |
| 4 | ገመድ ሸርቆሌ | 9 | አጋዬ አሸሸል | 14 | አሸሽቆ | 19 | አወልቤጉ |
| 5 | ጊዜ አጣርያ | 10 | መቃዘን | 15 | አሞርማ | | |

### ሸ) ቡልዲግሉ ወረዳ ስር

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ቡልድግሉ 01 | 9 | ቤልፀሪ | 17 | ቤልሚሊ | 25 | አልፈፍሽር |
| 2 | ቡልድግሉ 02 | 10 | ፍዱኒ | 18 | ቤላዳሩ | 26 | ቂዶ |
| 3 | ቡልንጆሮ | 11 | ምልንዱ | 19 | ቂዶሾንሾል | 27 | ዙምባ 02 |
| 4 | ቤላጋንዳ | 12 | ቤለዱሺ | 20 | ኩንፊ አርባ | 28 | አቡልጎዶ |
| 5 | አባንጎ | 13 | ቡልጵሊ | 21 | ቤልፍዲ | 29 | ባሚዜ |
| 6 | ዱሊ | 14 | ዮንጊ | 22 | መገሴ | 30 | አሁሩንጉ |
| 7 | ቡጺ | 15 | ጀንፊራሬ | 23 | ዙምባ 01 | | |
| 8 | ሆቢ | 16 | አልክሻፍ | 24 | ዳርዣሀብ | | |

### ቀ) ማኦ እና ኮሞ ልዩ ወረዳ ስር

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ቶንጎ 01 | 10 | ከሴር መ/2 | 19 | ጓቋ | 28 | ካዎ ሹመቴ |
| 2 | ዋንጋ ጊተን | 11 | ፁልጎሎ | 20 | ዜባ | 29 | ላቂ |
| 3 | ታጃ | 12 | ኮኮብ | 21 | ሾምቦላ | 30 | ሜጢ |
| 4 | ሾሾር | 13 | ዘብሸር | 22 | ፉፉ | 31 | በዴሳ |
| 5 | ዌዔ | 14 | ፔንሺባ | 23 | እሽጎጎ | 32 | ሹመቴ |
| 6 | ቱሉ | 15 | ጉሬ | 24 | ኩሳየ | 33 | ኡስጊንግላ |
| 7 | ሚሚ ያኮቦ | 16 | ያኣ ቤልዲግስ | 25 | የንጉ | 34 | ቶንጎ 02 |
| 8 | ቦቦስ እሽቀባ | 17 | ያያራ | 26 | ጋንዞ | | |
| 9 | ከሴር መ/1 | 18 | ባንጋ ተርኮ | 27 | ይዋ | | |

## በ) በዳንጉር ወረዳ ስር

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ማንቡክ 01 | 9 | ድልሳንቢ ኮከል | 17 | ድችሚያ | 25 | ቻምች |
| 2 | ማንቡክ 02 | 10 | ጅምትያ | 18 | አይሲካ | 26 | ንጉሰ ዳዊት |
| 3 | አዛርቲ ኪ.ትሊ. | 11 | ችዳንጉያ | 19 | ቆታ | 27 | ሳንጃ ባርክቶች |
| 4 | ማንቡክና ኪ.ትሊ. | 12 | ጉብላክ | 20 | አንጃ ኳያ | 28 | በረንጃ |
| 5 | ድምጻዬ በለስ ቁ.2 | 13 | ድባጢ | 21 | ዳንጉር ሚካኤል | 29 | ቡርጅ |
| 6 | አይፖፖ | 14 | ባውላ | 22 | ደቅ ማርያም | 30 | አንካሻ ገብርኤል |
| 7 | ጊጊ | 15 | ጁራይሲስ | 23 | አባይዳር | | |
| 8 | ዳቡኮከል | 16 | ዳጭግሪ | 24 | ጃባ | | |

## ተ) በማንዱራ ወረዳ ስር

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ግድም ዳሬሊ | 6 | ጅግዳ | 11 | ጉማዶ | 16 | ዳኍ ጉብሻ |
| 2 | ቱኒ ዳዶሽ | 7 | ኤዲዳ | 12 | ገነተ-ማሪያም | 17 | ዳኍአንዝባጉና |
| 3 | ኤጀንታ | 8 | ውዲት | 13 | ባቢሳ | 18 | ሳሀ ዳሀ |
| 4 | ዳች ሉምብያ | 9 | ድኩል | 14 | ፎቶ ማንጃሪ | 19 | ኤዲዳ ቁ.2 ማዕከል |
| 5 | ዳኍ ማክሰኝት | 10 | ዳቡሀ | 15 | ባሁስ | 20 | ዳፍላ |
| | | | | | | 21 | ኤሲ፻ |

## ቸ) በጉባ ወረዳ ስር

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ማንኩሽ | 6 | ጃድያ | 11 | አስዋር | 16 | አቡልታ |
| 2 | ያሬንጃ | 7 | ፋንጉሶ | 12 | ቤንጎ | 17 | ኦሜድላ |
| 3 | ባቢዘንዳ | 8 | ባምዛ | 13 | አብልሆርስ | | |
| 4 | ባሻታ | 9 | አልመሀል | 14 | አይንሽምሽ | | |
| 5 | አይሲድ | 10 | ባቢሽንኮር | 15 | ወደልበሂድ | | |

### ኀ) በድባጤ ወረዳ ስር

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ድባጤ 01 | 10 | ቂዶሀ | 19 | ሙዝን | 28 | ቆርቃ |
| 2 | ድባጤ 02 | 111 | ዝግሀ | 20 | ጫሊያ | 29 | አልባሳ |
| 3 | አንግቶክ | 12 | ግርዝ | 21 | ኮመድ | 30 | ሶንቦሰሬ |
| 4 | ሳስ ማንዳን | 13 | ፓርዘይት | 22 | ላይ ማንዳን | 31 | ጫንጮ |
| 5 | ሞጋ | 14 | ሰጋቡና | 23 | በጫቲ | 32 | ውብግሽ |
| 6 | ሰርበን | 15 | ሞደርም | 24 | ጊጰ | 33 | ታች ዶንበን |
| 7 | ጎንቻ | 16 | በርበር | 25 | ቱስኪጋምቤላ | 34 | ገፈሬ |
| 8 | ገሠስ | 17 | ዶንበን | 26 | ጋሴሳ | | |
| 9 | ያምፕ | 18 | ጉልፈን | 27 | ጃን | | |

### ነ) በቡለን ወረዳ ስር

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ቡለን 01 | 7 | ኤማንጅና ጎጃ | 13 | ማጣና ባጹሪ | 19 | ዶቢ |
| 2 | ቡለን 02 | 8 | በዶሬ | 14 | አዲስ አለም | 20 | ጎዶራሬ |
| 3 | መቲና ጊሳ | 9 | ኮሽ የጓንች | 15 | ሞራና ኤኩሳቂ | 21 | ኤቆንጢ |
| 4 | አዜምና በኖሽ | 10 | አይጋሊ ሞዘምቢስ | 16 | ጎንጎ | 22 | ግቺ ዱኩይ |
| 5 | ዶሽና ሞች | 11 | ባሩዳ | 17 | ጭላንቆ | | |
| 6 | በኩጅ | 12 | ሞጅንብ | 18 | ኤጳር | | |

### ኘ) በወምበራ ወረዳ ስር

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ክታር | 10 | ማንጎ | 19 | ሳንቂ | 28 | ጃድያ |
| 2 | ገሠገሳ | 11 | ደብረ ዘይት 01 | 20 | አድስ-አለም | 29 | ሀረቡ |
| 3 | ደብረ ዘይት 02 | 12 | ሙዝ | 21 | ቱሚ | 30 | አሽምብነት |
| 4 | ወግዲ | 13 | ዘማትያ | 22 | ጎቸር | 31 | ቦለስ |
| 5 | ኤጠሹሞ | 14 | ፒሬ | 23 | ኤበች | 32 | አይሺ |
| 6 | መነስቡ | 15 | በጎንዲ | 24 | ዱራ | 33 | ባዴሳ ኩሳየ |
| 7 | ነገር-ኮምጳ | 16 | አምቢፊታ | 25 | ሠንኮራ | 34 | ጀመራ |
| 8 | ኡቢ | 17 | ጋውሳ | 26 | ጫንጬ | 35 | ኪስያ |
| 9 | ዋቦ-አባይ | 18 | መልካን | 27 | ሚንጆ | 36 | ጎጀም-ሴሴ |

### አ) በፓዌ ወረዳ ስር

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | መድን | 7 | ቀ.1 መንደር 104 | 13 | ቀ.2 መንደር 21 | 19 | ቀ.1 መንደር 49 |
| 2 | ቀ.2 መንደር 28/29 | 8 | ህዳሴ | 14 | ቀ.2 መንደር 26 | 20 | ቀ.1 መንደር 127 |
| 3 | ፈለገ ሰላም | 9 | ፓዌ ከተማ 01 | 15 | መንደር 24 | 21 | መንደር 50 |
| 4 | አልሙ | 10 | ቀ.2 መንደር 17 | 16 | ቀ.2 መንደር 12 | 22 | መንደር 10 |
| 5 | ቀ.2 መንደር 134 | 11 | አባይ በር | 17 | ቀ.2 መንደር 14 | 23 | ፓዌ ከተማ 02 |
| 6 | ቀ.2 መንደር 30 | 12 | ቀ.2 መንደር 1 | 18 | ቀ.2 መንደር 23/45 | | |

### ከ) በካማሽ ወረዳ ስር

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | በገዴር | 5 | ቼድም | 9 | ኩጅ ዲዋ | 13 | መችኤኒያ |
| 2 | ፍሪንዥ | 6 | ኤየጃ | 10 | ማቆራ | | |
| 3 | ጋንጉጃ | 7 | ጋውል ደዛ | 11 | ቸች ጋዝ | | |
| 4 | ዠዎሽ | 8 | ዳንዝ ደዛ | 12 | ቅርዥዲዋ | | |

### ኸ) በዳምቤ ወረዳ ስር

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሚንፁቅ | 5 | ግሽመላ | 9 | ግች ሥዳ | 13 | ኤውዛኔያ |
| 2 | ኬንታ | 6 | ዳሺዳ | 10 | ጋጫያ | 14 | ደገናሃ |
| 3 | ሻንጂ ድማ | 7 | ጅዣና | 11 | ዳል | | |
| 4 | ግች ቦዋ | 8 | ግችዲዋ | 12 | ኦቾቅ | | |

### ወ) በሰዳል ወረዳ ስር

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ዲዛ | 5 | ኀካያ | 9 | ኤፀገዳ | 13 | ገችጃል |
| 2 | ቸስጋ | 6 | ሻዋ | 10 | ዝምጳ | 14 | ኳኛ |
| 3 | ትንጋ | 7 | መጉቻይ | 11 | ባፓራሮ | 15 | በንተርስ |
| 4 | መዳሌ | 8 | ግሽዣና | 12 | አድንቅሽ | | |

### ዐ) በምዥጋ ወረዳ ስር

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ታሶክ | 4 | አጌጼንቱ | 7 | አይሻንጂዲም | 10 | አይዣና |
| 2 | አይሻዋጅ | 5 | አይ ጃፕ | 8 | እምፑዋይ | 11 | ምዥጋ |
| 3 | ኤቦንጉይድ | 6 | ዌሪንቃ | 9 | ዳምቤ | 12 | ግች ገዴያ |

**ዘ) ዛይ ወረዳ ስር**

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ዛይ ዱውኤባ | 4 | አምባበስ | 7 | ግሽ ገፊቃ | 10 | አያምሳ |
| 2 | ግሽመላ | 5 | አያ ጠሸ | 8 | ግች ስያ | 11 | ዳንጉጽ |
| 3 | ኪግሻ | 6 | ኤዝቻቂ | 9 | ሻንኮማ | | |

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ስር እውቅና የተሰጣቸው ቀበሌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ሌሎች በአንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 2 የተመለከተውን የሚያሟሉ ቀበሌዎች ሊቋቋሙ ይችላሉ፡፡ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡

**<u>አንቀጽ 10</u>**

**<u>የአካባቢ አስተዳደር አካላለል የወሰንና የስያሜ ለውጥ</u>**

1. የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት በአዋጅ የአካባቢ አሰተዳደሮችን ወሰን ለማቋቋም፣ለመለወጥ፣ለማዋሐድ እንዲሁም እንደገና ለመከለልና ለማፍረስ የስም ስያሜ ለመለወጥ ይችላል፡፡
2. የወረዳ አሰተዳደር በአካባቢው አስተዳደር ውስጥ የሚገኙ የቀበሌዎች ወሰን የሚከለልበትን፣ የሚለወጥበትን፣ የሚዋኸድበትንና የሚፈርስበትን ተገቢ መረጃና የውሳኔ ሃሳብ አግባብነት ላለው በሕግ ሥልጣን ለተሰጠው አካል ያቀርባል፡፡
3. ከላይ በንዑስ ቁጥር 2 ሥር ስለሚቀርበው መረጃና የውሳኔ ሃሳብ ወረዳው የሚመለከታቸውን የቀበሌ ነዋሪዎች በቅድሚያ ማወያየትና ማማከር ይኖርበታል፡፡
4. የክልሉ ምክር ቤት አንድን የአካባቢ አስተዳደር ለማቋቋም ወይም ለመከፈል የሚያስችሉጥናቶችንና ሪፖርቶችን ከክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት፣ ከክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ፣ ከክልሉ የሰላም ግንባታና ፀጥታ ቢሮ እንዲቀርብለት ሊያደርግ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 11

## የወረዳና የቀበሌ አካባቢ አስተዳደሮች ማቋቋሚያ መስፈርት

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9 ላይ ያለው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ አዳዲስ የወረዳና ቀበሌ አስተዳደር አካባቢ ለመመስረት የሚከተሉት መስፈርቶች መሟላት አለባቸው፡-

1. ለወረዳ አሰተዳደር
   ሀ) ከ50,000 በላይ የሕዝብ ብዛት ያለው፤
   ለ) አካባቢውን ለማስተዳደርና አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችለውን የወረዳውን በጀት 25% ለመሰብሰብ የሚችል፤
   ሐ) የሕዝቡ አሰፋፈር አገልግሎት ለመስጠት ምቹ መሆኑ፤
   መ) የነዋሪው ሕዝብ ታሪካዊ አመጣጥ፣ባህልና ፍላጎት ናቸው፡፡
2. ለቀበሌ አስተዳደር
   ሀ) ከ5,000 በላይ የሕዝብ ብዛት ያለው፤
   ለ)የሕዝቡ አሰፋፈር አገልግሎትን ለመስጠት ምቹ መሆን ናቸው፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ  አንቀጽ 1 ፊደል ተራ “ሀ” ላይ የተደነገገዉ የህዝብ ብዛት መስፈርት ቢኖርም የክልሉ ምክር ቤት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘዉ በልዩ ሁኔታ የአካባቢው መልክዓምድራዊ አቀማመጥ ምቹነት ለመፍጠር፣የህዝብ አሰፋፈር፣ማኀበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችን ግምት ዉስጥ በማስገባት እና በጥናት በመለየት ከተገለጸው ቁጥር በታች የሆኑ የወረዳ አስተዳደሮችን  ሊሰይምና ሊያቋቁም ይችላል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ  አንቀጽ 2 ፊደል ተራ “ሀ” ላይ የተደነገገዉ የህዝብ ብዛት መስፈርት ቢኖርም የክልሉ መንግስት ምክር ቤት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘዉ በልዩ ሁኔታ የአካባቢው መልከዓምድራዊ አቀማመጥ ምቹነት ለመፍጠር፣የህዝብ አሰፋፈር፣ማኀበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችን ግምት ዉስጥ በማስገባት እና በጥናት በመለየት በተጨማሪ ቀበሌ አስተዳደሮችን  ሊሰይምና ሊያቋቁም ይችላል፡፡

## አንቀጽ 12

## የወሰን ለውጥና ምርጫ

ከላይ በአንቀፅ 10 ሥር በተደነገገው የአካባቢ አስተዳደር የወሰን ለውጥ ሲደረግ ለብሄራዊ የምርጫ ቦርድመገለጽ ይኖርበታል፡፡

## አንቀጽ 13

## የአካባቢ አስተዳደሮች ስያሜያቸውን መወሰን ስለመቻላቸው

1. አዲስ የአካባቢ አስተዳደር ሲመሰረት አዲሱ ምክር ቤት የአካባቢውን አስተዳደር ሥም መወሰንና መለወጥ ይችላል፣
2. ማንኛውም አዲስ ሥያሜ በክልሉ ወይም በአካባቢው አግባብነት ባለው ጋዜጣ ታትሞ መውጣት ይኖርበታል፣
3. ከላይ በንዑስ ቁጥር 1 እና 2 አዲስ የአካባቢ አሰተዳደር ሲሰየም የነባር አካባቢ አስተዳደር ሃብቶችና ዕዳዎች እንዲሁም መብቶችና ግዴታዎች ይተላለፋለታል፡፡

## አንቀጽ 14

## የወሰን አለመግባባቶች

በአካባቢ አስተዳደሮች መካከል የሚነሳ ማንኛውም የአካባቢ አከላለል አለመግባባትና የይገባኛል ጥያቄ በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ውሳኔ ያገኛል፡፡

## አንቀጽ 15

## የከተማ አስተዳደር አመሰራረት

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ምክር ቤት በከተማ አስተዳደር አዋጅና በዚህ አዋጅ መሰረት ከሚመለከተው የአካባቢ አስተዳደር ጋር በመመካከር በክልሉ መስተዳደር ምክር ቤት በኩል በተደረጉት ጥናቶች በመመስረት አንድ አካባቢ ከተማ የከተማ አስተዳደር ደረጃ እንዲኖረው ለመወሰን ይችላል፡፡

## አንቀጽ 16

## በአካባቢ አስተዳደር አካባቢዎች መካከል የሚደረግ ትብብር

1. ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ የአካባቢ አስተዳደሮች ትብብር ለማድረግ፣የተለየ አካል ለማቋቋም፣ለጋራ ልማት የሚውል ገንዘብ ለማዋጣት፣ልማትን ለማፋጠንና አገልግሎት ለመስጠት የሚደረገውን ጥረት የሚያስተባብሩ ፅህፈት ቤቶች ሊመሰርቱ ይችላሉ፣
2. ከላይ በንዑስ ቁጥር 1 የተገለፀው ስምምነት ለክልሉ መስተዳድርምክር ቤት ቀርቦ መፅደቅ ይኖርበታል፡፡

## ክፍል ሦስት

## የአካባቢ አሰተዳደሮች የመንግሥት አካላትና ስብጥር

## አንቀጽ 17

## የወረዳ አስተዳደር አካላት

የወረዳ አካባቢ አስተዳደር የወረዳ ምክር ቤት፣የወረዳ መስተዳድር ምክር ቤት እና የዳኝነት አካላት ይኖራቸዋል፡፡

## አንቀጽ 18

## የወረዳ ምክር ቤት አባላት

1. እያንዳንዱ ወረዳ የራሱ ምክር ቤት የሚያቋቁም ሲሆን አባላቱ ተጠሪነታቸው ለመረጣቸው ህዝብ ይሆናል፡፡
2. የወረዳ ምክር ቤት አባላት ወረዳው የተደራጀበት አካባቢ ከሚገኙት የቀበሌ ነዋሪዎች መካከል በቀጥታ በህዝብ የሚመረጡ ይሆናሉ፡፧
3. ሁሉም የወረዳው ምክር ቤት አባላት ድምፅ የመስጠት መብት አላቸው፡፡

## አንቀጽ 19

## የወረዳ ምክር ቤት አባላት ተግባርና ሃላፊነት

አንድ የምክር ቤት አባል የሚከተሉት ተግባርና ሃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

1. ከመረጠው ህዝብ ጋር በቅርበት እየተገናኘ ለምክር ቤቱ ለውይይት በሚቀርቡ ሃሳቦች ላይ የመረጠው ህዝብ እንዲወያይበት ያደርጋል፤
2. በምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ እንደአስፈላጊነቱ ሃሳብ፣ አስተያየትና የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፤
3. በማንኛውም የምክር ቤቱ ስብሰባ የመገኘትና ተመድቦ በሚሰራበት ኮሚቴ ይሳተፋል፤
4. ከመረጠው ህዝብ ጋር ውይይት የሚያደርግበትን ቀነ-ቀጠሮ አስቀድሞ ያዘጋጃል፤
5. በምክር ቤቱ ስብሰባዎች ላይ የተካሄዱአጠቃላይ ውይይቶችና በመራጩ አካባቢ የተነሱ ችግሮችን ለመፍታት የተወሰዱ እርምጃዎችን በሚመለከት ለመራጩ አካባቢ ህዝብ ሪፖርት ያሳውቃል፤
6. በወረዳ በአጠቃላይና በተለይም በተመረጠበት አካባቢ በሚካሄዱ ልማታዊ እንቅስቃሴዎች ይሳተፋል፤
7. ሃላፊነቱን በሚወጣበት ጊዜ ለብሄራዊ ጥቅሞች ቅድሚያና ትኩረት ይሰጣል፡፡

## አንቀጽ 20

## ለተመራጭነት ብቁ የሚያደርጉ መስፈርቶች

1. ለወረዳ ምክር ቤት አባልነት የሚያበቁ መስፈርቶች በዚህ አዋጅና በምርጫ ህጉ ላይ የተዘረዘሩ ለምርጫ ብቁ የሚያደርጉ መስፈርቶች ይሆናሉ፡፡
2. የእያንዳንዱ የወረዳ ምክር ቤት አባላት ቁጥር በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤትና በብሄራዊ ምርጫ ቦርድ የወረዳውን ህዝብ ቁጥር መሰረት በማድረግ የሚወሰን ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 21

## የምክር ቤት አባላት የሥራ ዘመን

1. የእያንዳንዱ ምክር ቤት አባል የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ነው፡፡
2. የአምስት ዓመቱ የሥራ ዘመን ከመጠናቀቁ በፊት የማሟያ ምርጫ የሚደረግ ከሆነ የተመራጩ ምክር ቤት አባል የሥራ ዘመን ቀሪው የምክር ቤቱ ሥራ ዘመን ይሆናል፡፡
3. የአንድ የምክር ቤት አባል ወምበር በማንኛውም ምክንያት ክፍት በሚሆንበትጊዜ ለቀሪው ሥራ ዘመን ምርጫ የሚካሄደው፡-

ሀ) ወምበሩ ክፍት መሆኑ ከታወቀበት ጊዜ ጀምሮ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥይሆናል፤

ለ) ቀሪው የሥራ ዘመን ከአንድ ዓመት በታች ከሆነ የማሟያ ምርጫአይደረግም፡፡

## አንቀጽ 22

## ድምፅ የማይሰጡ ተሳታፊዎች

በወረዳ ምክር ቤት ስብሰባ ድምፅ ሳይኖራቸው የሚሳተፉ አባላት፡-

1. የወረዳው ምክር ቤት አባላት ያልሆኑ የወረዳው መስተዳድር ምክር ቤት አባላት፤
2. የሁሉም ቀበሌ አስተዳዳሪዎችና አፈ-ጉባኤዎች፤
3. የወረዳው ፍርድ ቤት ሃላፊዎች፤
4. የወረዳው ምክር ቤት አባላት ያልሆኑ የወረዳው አስፈፃሚ መስሪያ ቤትወይም ፅህፈት ቤት ሃላፊዎች፤
5. የከተማ አስተዳደር ከንቲባዎችና ምክትል ከንቲባዎች፤
6. በወረዳው የምርጫ ክልል ለክልል ምክር ቤት የተመረጡ የክልል ምክር ቤት አባላት፤
7. በምክርቤቱ ስብሰባ እንዲካፈሉ በአፈ-ጉባኤው የሚጋበዙ የሲቪል ማህበረሰብ፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የህዝባዊ ድርጅቶች ተወካዮች ናቸው፡፡

## አንቀጽ 23

## የወረዳው ምክር ቤት አባላት ሥነ-ምግባር

የወረዳ ምክር ቤት አባላት ሥነ-ምግባርና የአሰራር ሥነ-ሥርዐት በወረዳው ምክር ቤት በሚወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

## አንቀጽ 24

## የወረዳ አፈ-ጉባኤ ሥልጣንና ተግባር

የወረዳው አፈ ጉባኤና ምክትል አፈ ጉባኤ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሯቸዋል፡፡

1. አፈ-ጉባኤው፡-

   ሀ) በተቀመጠው የሥብሰባ ጊዜ መሰረት ምክር ቤቱን ይሰበስባል፣ ስብሰባውንም ይመራል፤

   ለ) በዚህ አዋጅ መሰረት የምክር ቤቱን አሰቸኳይ ስብሰባዎች ይጠራል፣ ይመራልም፤

ሐ) ምክር ቤቱን በሦስተኛ ወገኖች ዘንድ ይወክላል፤

መ) ምክር ቤቱ በአባላቱ ላይ የሚወስደውን የዲሲፕሊን እርምጃ ያስፈፅማል፤

ሠ) የምክር ቤቱን ቋሚና ጊዚያዊ ኮሚቴዎች ያስተባብራል፤

ረ) ምክር ቤቱን ወክሎ የምክር ቤቱን አስተዳደራዊ ጉዳዮች ይመራል፤

ሰ) በምክር ቤቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፤

2. ምክትል አፈ-ጉባኤ፡-

ሀ) በአፈ-ጉባኤው ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፤

ለ) አፈ-ጉባኤው በማይኖርበት ጊዜ ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ወይም አቋም ይዞ ለመከራከር ሲፈልግ ምክትል አፈ-ጉባኤው ተክቶ ይሰራል፡፡

## አንቀጽ 25

## የምክር ቤት አባልነት የሚቋረጥበት ሁኔታ

የወረዳ ምክር ቤት አባልነት በሚከተሉት ሁኔታዎች ሊቋረጥ ይችላል፡-

1. በህገ-መንግስቱና በምርጫ ህጉ ላይ የተዘረዘሩት ለተመራጭነት ብቁ የሚያደርጉ መመዘኛዎችን አለማሟለቱ ሲረጋገጥ፤
2. አባሉ የተመረጠበት ወረዳ ሲከፈል ወይም ሲዋኸድ፤
3. የወረዳ ምክር ቤት አባሉ ለክልል ወይም ለፌደራል ምክር ቤት አባልነት ሲመረጥ፤
4. አባሉ ያለበቂ ምክንያት በተከታታይ በአራት ስብሰባዎች ያልተገኘ እንደሆነ፡፡ ይህ በቂ ምክንያት ተቀባይነት የሚያገኘው የምክር ቤቱ አባላት ባንድነት አባሉ ያቀረባቸውን ምክንያቶች ካዳመጡ በኂላ በሚሰጡት ውሳኔ መሰረት ይሆናል፤
5. አባሉ በሙስናና በሌሎች ወንጀሎች ተከሶ የአንድ ዓመት እስራት እንዲቀጣ ከተፈረደበትና ከታሰረ፤
6. የምክር ቤቱ አባል በራሱ ውሳኔ ከምክር ቤቱ አባልነት ሲለቅ፤
7. አግባብ ባለው ህግ መሰረት የምክር ቤቱ አባል በመረጠው ህዝብ ከአባልነት እንዲነሳ ሲወሰን፤

8. በሞት ወይም ችሎታ በማጣት፤

9. በዚህ አዋጅ አንቀፅ 10 መሰረት ምክር ቤቱ ሲበተን ናቸው፡፡

## አንቀጽ 26

## ዋና አስተዳዳሪ

1. እያንዳንዱ ወረዳ በምክር ቤቱ አብላጫ መቀመጫ ካለው የፖለቲካ ፖርቲ ወይም ፓርቲዎች መካከል በምክር ቤቱ አባላት መካከል በምርጫ የሚሠየም ዋና አስተዳዳሪ ይኖረዋል፡፡
2. አግባብነት ያለው የሌላ ህግ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የወረዳው ዋና አስተዳዳሪ ተጠሪነት ለወረዳው ምክር ቤትና ለክልሉ ርዕሰ-መስተዳድር ነው፡፡
3. የዋና አስተዳዳሪው የሥራ ዘመን ከወረዳው ምክር ቤት የሥራ ዘመን ጋር እኩል ይሆናል፡፡
4. ዋና አስተዳዳሪው ለምክር ቤቱ ከሶስት ወር በፊት በጽሁፍበማሣወቅ በገዛ ፈቃዱ ኃላፊነቱን ሊለቅ ይችላል፡፡
5. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 4 ላይ ያለው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና አስተዳደሪው በችሎታ ማነስ፣ በዲሲፒሊን ወይም በሥነ-ምግባር ብልሹነት ወይም በወንጀል የሚያስከስስ ጥፋት ፈፅሚል ተብሎ ሲጠረጠር ከኃላፊነቱ ታግዶ ጉዳዩ በምክር ቤቱ ይወሰናል፡፡ ዝርዝሩ ይህን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡

## አንቀጽ 27

## የወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት /ካቢኔ/

በክልሉ ህገ-መንግሥት አንቀፅ 91 መሠረት የወረዳው ምክር ቤት ለራሱ ተጠሪ የሆነ የወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት ይኖረዋል፡፡

## አንቀጽ 28

## ስለ ወረዳው አስተዳደር ምክር ቤት አባላት

1. የወረዳው አስተዳደር ምክር ቤት አባል መሥሪያ ቤቶችን በተመለከተ ዝርዝሩ በህግ የሚወሰን ሆኖ የስራ ባህሪና ስፋት የወረዳውን የገንዘብ መጠንና ገቢ የመሠብሠብን አቅም ግምት ውስጥ በማስገባት ይሆናል፡፡

2. የወረዳው አስተዳደር ምክር ቤት የሚከተሉትን አባላት ያካትታል፡-

   ሀ) ዋና አስተዳደሪ፤

   ለ) በዋና አስተዳዳሪ ተመርጦ በወረዳው ምክር ቤት የሚሾም ምክትል አስተዳዳሪ፤

   ሐ) በዋና አስተዳዳሪ ለወረዳው አስተዳደር ምክር ቤት አባልነት ተመርጠው በወረዳ ምክር ቤት ሹመታቸው የሚፀድቁ አባላት፡፡

3. የወረዳው አስተዳደር ምክር ቤት አባላት ሹመት የሴቶችንና የወጣቶችንተሣትፎየሚያረጋግጥናየአካልጉዳተኞችንየሚያበረታታመሆንአለበት፡፡

4. የወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት አባላት ኃላፊነት፣ ደመወዝ፣ የዲሲፒሊን እርምጃ አፈፃፀም ሥርዓት እና የአሠራር አቅጣጫዎች በክልል መስተዳድር ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡

5. የወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት የሥራ ዘመን ከወረዳ ምክር ቤት የሥራ ዘመን ጋር እኩል ይሆናል፡፡

6. የወረዳው አስተዳደር ምክር ቤት አባላት ከሶስት ወር በፊት ለዋናው አስተዳደሪው በጽሁፍ በማሣወቅ በራሳቸው ፈቃድ ኃላፊነታቸውን መልቀቅ ይችላሉ፡፡

7. አንድ የወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት አባል በችሎታ ማነስ፣ በሥነ -ምግባር ግድፈት ወይም በከባድ ወንጀል ሲጠራረጠር ከኃላፊነቱ ሊነሣ ይችላል፡፡

## <u>አንቀጽ 29</u>

## <u>ቋሚ ኮሚቴዎች</u>

የወረዳ ምክር ቤት ኃላፊነቱን ለመወጣት የሚያግዙ እያንዳንዳቸው ከሶስት ያላነሱ አባላትን ያቀፈ ቋሚ ኮሚቴዎችን የሚያቋቁም ሲሆን፡-

1. የቋሚ ኮሚቴዎች ተጠሪነት ለወረዳው ምክር ቤትና ለአፈ-ጉባኤው ነው፡፡
2. የቋሚ ኮሚቴ አባላት አመራረጥ፣አመራር፣ ብዛት፣ የስብሠባ ሥነ-ሥርዓትና የስብሰባ ጊዜ በወረዳው ምክር ቤት በሚወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡
3. የቋሚ ኮሚቴዎች የተጣለባቸውን የመቆጣጠርና የመከታተል ኃላፊነት በህግ ተለይቶ በሚሠጣቸው መሥሪያ ቤቶች የሚያከናውኑ ሲሆን በዋና ዋና ጉዳዮች ማለትም፡-

   ሀ) የሐገሪቱ የክልሉና የወረዳው ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ እቅዶች ህጉችና አሠራሮች በወረዳው ውስጥ በተግባር ላይ ስለመዋላቸውና በተቀመጠው አቅጫጫ ስለመፈፀማቸው፤

ለ) የወረዳውን በጀትና ሐብትን በተመለከተ በትክክል በሥራ ላይ በታለመበት መልኩ ስለመዋሉ፤

ሐ) የዜጐች መብቶችና ነፃነቶች በወረዳው መከበራቸውን ተከታትለው የሚያስፈፅሙ መሆን አለባቸው፡፡

## አንቀጽ 30

## ሌሎች ኮሚቴዎች

በወረዳው ምክር ቤት አንድን የተለየ አላማ ለማከናወን የተለየ ኮሚቴ /ጊዜያዊ፣ንዑስና ሌላ/ ሊያቋቁሙ ይችላል፡፡ የኮሚቴው አባላት የሚመሩበት ሥርዓት ሥልጣንና ተግባራቸው በምክር ቤቱ በሚወጣው መመሪያ የሚወሰን ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 31

## የወረዳ ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

የወረዳው ምክር ቤት በክልሉ ህገ-መንግሥት አንቀጽ 87 የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አንቀጽ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. ከምክር ቤት አባላት መካከል ዋና አስተዳደሪውን ይመርጣል፣የምክትል አስተዳዳሪውንና የአስተዳደር ምክር ቤት አባላትን ሹመትያፀድቃል፣ የሚመሯቸውን መስሪያ ቤቶች ይወስናል፤
2. በክልል መስተዳድር በየጊዜው የሚወጡ ደንቦችንና መመሪዎችን ያስፈፅማል፤
3. በክልሉየልማት ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና እቅዶች ላይ በመመስርት የወረዳውን ስትራቴጂያዊ የልማትና አመታዊ እቅዶች የህዝቡን ተሣትፎ ባካተተ መልኩ መዘጋጀታቸውን ያረጋግጣል፤
4. ህብረተሰቡ በልማት እቅዶች አዘገጃጀት፣አፈፃፀምና በግምገማ ሂደት እንዲሣተፍ ያደርጋል ያበረታታል፤
5. በተለየሁኔታወረዳውን የሚመለከት መሆኑ በክልል የልማት ፕሮጀክት እቅድና ተግባራት ተለይተው የተቀመጡትን ጉዳዮች በወረዳው እቅድ ውስጥ መካተታቸውን ያረጋግጣል፤
6. የወረዳውን የልማት እቅደች ያፀድቃል፤

7. በወረዳው አስተዳደር ምክር ቤቱ የሚቀርቡለትን ፕሮጀክቶች ፕሮግራሞችና እቅዶች ቅድሚያ መሠጠት ያለባቸውንና አዋጭነታቸውን ያረጋግጣል፤
8. ለእቅዶችና ፕሮግራሞች ተግባራዊነት ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
9. የወረዳውን በጀት ያፀድቃል፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፤
10. በህግ ተለይቶ በተሠጠው ሥልጣን ውስጥ የወረዳው አስተዳዳር ምክር ቤት በየሚያቀርብለት የግብር፣ የአገልግሎት ክፍያና ቀረጥ አከፋፋል በውሳኔ አስተያየት መሠረት ይወሰናል፤
11. በወረዳው እቅዶችና በጀት አፈፃፀም ላይ ክትትልና ቁጥጥር ያካሂዳል፣ በአፈፃፀሙ ውጤት መሠረት ተገቢውን ውሳኔ ይወስናል፤
12. የዋናአስተዳዳሪውን፣የአስተዳደር ምክር ቤቱንና የሌሎች ባለሥልጣናትን የሥራ አፈፀፀም ይከታተላል፣ ይገመግማል፤
13. ከወረዳው አስተዳደር ምክር ቤትና ከምክር ቤቱ የበጀትና ፋይናንስ የሚቀርብለት የኦዲት ሪፖርት ላይ ይወያያል፣አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል፤
14. ከአስተዳደር ም/ቤት በሚርቡለት ረመመሪያዎች ላይ ተወያይቶ ይወሰናል ተግባራዊ ያደርጋል፤
15. የወረዳውን ተፈጥሮ ሐብት አስተዳደር ይከታተላል፣ የዱር እንስሳትንና አእዋፍት ጥበቃና እንክብካቤ እንዲደረግላቸው ያበረታታል፤
16. በህገ-መንግስቱ ላይ ስለፍርድ ቤቶች የዳኝነት ነፃነት ድንጋጌዎች እንደጠበቁ ሆነው በወረዳው ፍርድ ቤት ሪፖርት ላይ ይወያያል፣ የሥራ አፈፃፀምን ይገመግማል፣ ለሚመለከተው አካልም አስተያየቱን ያቀርባል፤
17. የዚህ አዋጅ አንቀጽ 10 ወይም 2 እንደተጠበቀ ሆኖ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ከክልሉ መስተዳድር ከሚሰጠው አመራር አቅጣጫ መሠረት ከወረዳው በታች ያሉ አስተዳደሮችን መዋቅርና ወሰናቸውን እንደ አግባብነቱ ሊያስተካክል ይችላል፡፡ይህን ተግባር በሚያከናውንበት ጊዜ:-

    ሀ) አስተዳደራዊቅልጥፍናን፤

    ለ) መልክአ ምድራዊ አቀማመጥን፤

    ሐ) ለግንኙነትያለውን አመቺነት፤

    መ) የህዝቡንሁኔታና ብዛት፤

    ሠ) የሚመለከተውን ህዝብ ፈቃድ ከግመት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡

18. በሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ቀበሌዎች በሚነሱ የዲስፕሊን ክርክሮች ላይ ይወስናል፤
19. በክልሉ ከሚገኙ ወረዳዎችመካከልየሚነሱየወሰንና ተዛማች ክርክሮችን ለአስተዳደርና ፀጥታ ቢሮ ያቀርባል፤
20. ለአባላቱ የሥነ-ምግባር መመሪያ ያወጣል፤
21. በወረዳው ሰላም፣ ፀጥታ፣ ህግና ሥርዓት መከበሩን ያረጋግጣል፤
22.በስሩ ያሉ የቀበሌ ምክር ቤቶችን ያጠናክራል፣ ከተሰጠው ሥልጣንና ተግባርም የተወሰነውን ለቀበሌ ምክር ቤት በውክልና ሊሠጥ ይችላል::

## አንቀጽ 32

## የወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት ተግባርና ኃላፊነት

የወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት በሕገ-መንግሥት አንቀጽ 92 ከተሰጠው ሌላየሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች በተጨማሪ ይኖሩታል፡-

1. በዋና አስተዳደሪው የቀረቡለትን ከመስተዳድር ምክር ቤት አባላት ውጭ የሆኑ የሥራ ኃላፊዎችን ሹመት ያፀድቃል፤
2. በፌደራልና በክልል መንግሥት የወጡትን ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ እቅዶችና ፕሮግራሞች በወረዳው ውስጥ ተግባራዊ ያደርጋል፤
3. የወረዳውን ስትራተጂያዊ የልማት ዕቅድ በማዘጋጀት ለወረዳው ምክር ቤት ቀርቦለት ሲፀድቅም በተግባር ላይ ያውላል፤
4. የወረዳውን ዓመታዊ በጀት አዘጋጅቶ ለምክር ቤት ያቀርባል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤
5. የፌደራልና የክልል ስትራጂያዊ የልማት ዕቅድና ፖሊሲዎች የተካተቱበትን የወረዳውን ዕቅዶችና ፕሮግራሞች ያስፈጽማል፤
6. በወረዳ የሚከናወኑ ፕሮጀክቶችንና ፕሮግራሞችንአፈፃፀምም ክትትልና ግምገማ ያደርግባቸዋል፤
7. የወረዳ መሠረተ-ልማቶች ጥገና እንዲደረግላቸው ያደርጋል፤
8. በወረዳ የሚሰጡ ማህበየወረዳ አስፈፃሚ አካላትን ይቆጣጠራል፣ ይከታተላል፣ ሥራቸውንም በበላይነት ይመራል፤
9. የወረዳ አስፈጻሚ አከላትን ቆጣጠራል፣ይከታተላል፣ ስራቸውንም በበላይነት ይመራል፤

10. በሕግ ተለይቶ በተሰጠው መሠረት የገጠር መሬት መጠቀሚያ ግብር፣ የእርሻ ገቢ ግብርና የሌሎች ገቢዎች ግብር፣ መሰብሰቡን ያረጋግጣል፡፡ በተጨማሪ የገቢ ምንጮችን በማጥናት ለውሳኔ ለምክር ቤቱ ያቀርባል፤
11. የወረዳውን ሕብረተሰብ ሰላምና ፀጥታ ይጠብቃል፣ የፀጥታና ፖሊስ አካላትን ይመራል፣ ሥራቸውንም ይከታተላል፣ ይቆጣጠራልም፤
12. ሕብረተሰብን በማነሣሣት የገጠር ልማት ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፤
13. የወረዳውን የተፈጥሮ ሀብት በመጠበቅ ፍትሐዊ አጠቃቀም እንዲኖረው ዘላቂ ልማትን ያረጋግጣል፤
14. በወረዳው ውስጥ የሚገኙ ማናቸውንም ቅርሳቅርስ አስፈላጊ ጥበቃና እንክብካቤ እየተደረገለት ስለመሆኑ በቅርበት ይከታተላል፡፡ ለቀጣይ ትውልድም ጥቅም ላይ እንዲውል ያደርጋል፤
15. የክልልና የፌደራል ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች ተገቢነት የሌለው ራዊ አገልግሎቶችን በሚመለከት ክትትልና ግምገማ ያደርጋል፣ክንውንና ብልሹ አሠራር መኖሩን ሲያረጋጥ ለሚመለከተው መንግሥታዊ አካል ያሳውቃል፤
16. በተሰጠው ስልጣንና የበጀት ማእቀፍ መሠረት የፀደቁ ዕቅዶችን ተግባራዊ ለማድረግ ለበታች አስተዳደሮች፣ ማህበራትና ድርጅቶች ሃብት ይደለድላል፤
17. በተሰጠው ስልጣን መሠረት ከግለሰቦች፣ከመንግስታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ወይም ለምሣሌ የግንባታ ወዘተ ስምምነቶችን ያደርጋል፡፡ የዚህ ዓይነቶቹ ስምምነቶች የውጭና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር የሚደረግ ከሆነ ስምምነቶቹን የክልል መስተዳድር ምክር ቤት እንዲያውቀው ያደርጋል፤
18. በወረዳው ምክር ቤት የሚሰጡ ሌሎች ተግባራትንም ሆነ በክልሉ መንግሥት መስተዳድር ምክር ቤት በደንብ ወይም በሌላ ሕግ የሚሰጡትን የሥልጣን ውክልና ተቀብሎ ይፈጽማል፡፡

## አንቀጽ 33

## የወረዳ ዋና አስተዳዳሪ ኃላፊነትና ተግባራት

ዋና አስተዳደሪው የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

1. የወረዳን አስተዳደር ይወክላል፤

2. ምክትል አስተዳዳሪውን ጨምሮ የወረዳውን አስተዳደር ምክር ቤት አባላት ሹመት ለወረዳው ምክር ቤት አቅርቦ ያስፀድቃል፤

3. የምክትል አስተዳዳሪውንና የሌሎች የአስተዳደር ምክር ቤት አባላትና የአስፈፃሚ መስሪያ ቤቶች የሥራ አፈፃፀምንይቆጣጠራል፣ ይመራልም፤

4. የአስተዳደርምክርቤቱንና የሌሎች አስፈፃሚ አካላትን የሥራ አፈፃፀም ወቅታዊ ሪፖርት ለወረዳው ምክር ቤትና ለክልሉ ርዕሰ-መስተዳድር ያቀርባል፤

5. በጽ/ቤቱ ኃላፊ በኩል የአስተዳደር ምክር ቤቱን ስብሰባ ይጠራል፣ ይመራልም፤

6. በምክር ቤቱ የፀደቁ እቅዶችና በጀት በወረዳው አስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶች ተግባራዊ መደረጋቸውን ያረጋግጣል፤

7. የወረዳው ነዋሪ ህዝብ ሠላምና ደህንነት በአስተማማኝ ሁኔታ ይጠበቅ ዘንድ ህግንና ሥርዓትን እንዲያስከብሩ የተቋቋሙትን የፀጥታና የፖሊስ ኃይሎች በበላይነት ይመራል፤

8. የአስተዳደሩ የበጀት አጠቃቀም፣ የአገልግሎት አሠጣጥ እና የፋይናንስ አስተዳደር በህዝብ አገልጋይነት፣ በግልፀኝነትበተጠያቂነት እንዲሁም ከህዝብ ጋር በሚደረገው ይፋ ውይይት ላይ ተመስርቶ እንዲፈፀም ያደርጋል፤

9. ለቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት አባላት የሥራ እንቅስቃሴ ድጋፍ ይሠጣል፣ ሥራቸውንም ያስተባብራል፤

10. በክልሉ ምክር ቤት እና በርዕሰ-መስተዳድሩ የሚሠጡ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## <u>አንቀጽ 34</u>

## <u>የወረዳ ምክትል አስተዳዳሪ ሥልጣንና ተግባር</u>

1. ዋና አስተዳዳሪው በማይኖርበት ወይም ኃላፊነቱን መወጣት በማይችልበት ወቅት ተክቶ ይሠራል፣

2. በዋና አስተዳሪውና በወረዳው አስተዳደር ምክር ቤት ተለይተው የሚሠጡትን ተግባራት ያከናውናል፡፡

## <u>አንቀጽ 35</u>

## <u>የወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት አባላት ተግባርና ኃላፊነት</u>

የወረዳው አስተዳደር ም/ቤት /ካቢኔ/ አባላት የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት አላቸው፡-

1. የሚመሩትንመሥሪያቤትእቅድናበጀትበወረዳውየልማትእቅዶችናበጀቶችመሰረት መታቀዳቸውን ያረጋግጣል፤
2. የአስተዳደር ምክር ቤት አባሉ የሚመራው መሥሪያ ቤት የሥራ እንቅስቃሴን በሚመለከት የሴክተሩ ሥራ በቅልጥፍናና በውጤታማነት መፈፀሙን ክትትልና ግምገማ መካሄዱን ያረጋግጣል፤
3. የሚመራውን መሥሪያ ቤት የሥራ አፈፃፀም በሚመለከት ለአስተዳደር ምክር ቤቱ ወቅታዊ ሪፖርት ያቀርባል፣ ሪፖርቱም የፋይናንስ የፕሮጀክት ልማት እንቅስቃሴን፣ የበጀት አጠቃቀምን፣ የአገልግሎት አሠጣጥ አፈፃፀምን ማካተቱን ያረጋግጣል፤
4. በሚመራው መስሪያ ቤት የሥራ እንቅስቃሴ ላይ ለሚሣተፉ ለሁሉም የልማት ኃይሎች ማለትም የመንግሥት፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ፣ ለግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ እና ለሲቪልማህበረ-ሰብ አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል፤
5. በሚመራው ሴክተር የሕዝብ ተሳትፎን፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችንና ማህበረ-ሰብ ተኮር ድርጅቶች ተሳትፎን ለማረጋገጥ ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል፣ ያበረታታልም፤
6. የሚመራውን ሴክተር በሚመለከት በቀበሌና በከተማ አስተዳደሮች በሚደረጉ ውይይቶች ላይ ይሣተፋል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ለወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት ሪፖርት ያደርጋል፤
7. በዋና አስተዳደሪው የሚሰጡ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## አንቀጽ 36

## የወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤት ኃላፊ ተግባርና ሥልጣን

የወረዳ አስተዳዳሪ ጽ/ቤት ኃላፊ ተጠሪነቱ ለዋና አስተዳዳሪ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት አሉት፡-

1. ዋና አስተዳዳሪው ኃላፊነቱን ለመወጣት የሚያስችሉ የእለትተእለት አስተዳደራዊ ሥራዎችን ያከናውናል፤
2. የወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት የሥብሰባ ቃለ-ጉባኤ በሚገባ መያዙንና መጠበቁን ያረጋግጣል፤
3. የጽ/ቤቱን አመታዊ እቅድና በጀት አዘጋጅቶ ለዋና አስተደዳሪ ያቀርባል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤
4. የጽ/ቤቱን የሂሳብ አሠራርና ግዥዎች በመንግሥት የፋይናንስ ደንቦች መሠረት መከናወናቸውን ያረጋግጣል፤
5. ወቅታዊ የሆነ የእቅድ አፈፃፀምና የፋይናንስ ሪፖርት ለዋና አስተዳዳሪው፣ ለአስተዳደር ምክር ቤት አባላትና ለምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴዎች ያቀርባል፤
6. የጽ/ቤቱን ሠራተኞች በሲቪል ሰርቪስ ህግ መሠረት ይቀጥራል፣ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፤
7. የጽ/ቤቱን ቋሚና ተንቀሳቃሽ ንብረቶች ይጠብቃል፣ይንከባከባል፤
8. በአስተዳዳሪውና በምክር ቤቱ የሚሠጡ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## አንቀጽ 37

## ስለ ወረዳው አስተዳደር ሴክተር ጽህፈት ቤቶችና ተግባራት

1. የወረዳውአስተዳደር ተግባርና ኃላፊነቱን ለመወጣት የሚያስችሉት ሴክተር ጽ/ቤቶች ይኖሩታል፡፡
2. እነዚህን ሴክተር ጽህፈት ቤቶች የሚመሩ ኃላፊዎች የሚከተሉት አጠቃላይ ተግባራት ይኖሯቸዋል፡-
   ሀ) በየጽህፈት ቤቶቻቸው እስትራቴጂያዊና አመታዊ እቅዶችን ያዘጋጃሉ፤
   ለ) ከአስተዳደር ምክር ቤቱ ጋር በመቀናጀት አመታዊ በጀት ያዘጋጃሉ፣በሚመለከተውአካልሲፈቀድምተግባራዊያደርጋሉ፤

ሐ) የጽህፈት ቤታቸውን ሠራተኞች በሲቪል ሰርቪስ ህግ መሠረት ይመለምላሉ፣ ይቀጥራሉ፣ ያስተዳድራሉ፣ ያሰናብታሉ፤

መ) ጽህፈት ቤታቸውን በሚመለከት የወጡ ህጐች፣ ደንቦች፣ የሥራ አፈፃፀም ደረጃዎችና መመሪያዎች ተግባራዊ መሆናቸውን ያረጋግጣሉ፤

ሠ) የጽህፈት ቤታቸውን ስታስቲካል ዳታ ቤዝ ያቀናብራሉ፣ ይጠብቃሉ፣ ለሚመለከተው አካልም ያስተላልፋሉ፤

ረ) በጽህፈት ቤታቸው እቅድ ውስጥ ሥርዓተ-ጾታን ያካትታሉ፤

ሰ) የኤች.አይ.ቪ. ኤድስን የመላከላከልና የመቆጣጠር ፕሮግራም በጽህፈት ቤታቸው ስትራቴጂያዊና አመታዊ እቅድ መካተቱን ያረጋግጣሉ፤

ሸ) ለዋና አስተዳደሪው፣ ለወረዳው ምክር ቤት፣ ለክልል ሴክተር ቢሮ እና በመመሪያ ለተወሰነላቸው አካላት በየሩብ አመቱ ወቅታዊ ሪፖርት ያቀርባሉ፡፡

3. ከክልሉ ሴክተር ቢሮዎች ጋር የተጣጣመ የእቅድ ፣ የፕሮጀክትና የፕሮግራም የሥራ አፈፃፀም ቢጋር ያዘጋጃሉ፣ ይፈጽማሉም፤

4. የሴክተር ጽህፈት ቤት አጠቃላይ የሂሳብ አጠቃቀም በሴክተር ጽህፈት ቤቱ የውስጥ ኦዲትና በዋና የኦዲተር መሥሪያ ቤት ተገቢው ምርመራ ይደረጋል፡፡

## አንቀጽ 38

## የወረዳው ሴክተር መስሪያ ቤቶች አቋቋም

በክልሉ ሕገ-መንግሥትና በዚህ አዋጅ መሠረት ወረዳን ማዕከል ያደረጉ የወረዳአስተዳደር ተግባራት የሚያከናወኑ ጽህፈት ቤቶች ይቋቋማሉ፡፡ የጽህፈት ቤቶቹ ብዛትና ዝርዝር ተግባራት የክልሉን አስፈጻሚ አካላት ለማቋቋምና ተግባርና ኃሊፊነትን የሚወስነው ህግ በመከተልበሌላ ሕግ ይወሰናል፡፡

## አንቀጽ 39

## ቀበሌዎች

የቀበሌ አስተዳደርር የክልሉ የመጨረሻ መንግስታዊ የአስተዳደር እርከን ሲሆን በክልሉ ሕገ-መንግሥትና በዚህ አዋጅ መሠረት ተጠሪነቱ እንደ ሁኔታው ለታቀፈበት ወረዳ አስተዳደር ነው፡፡

## አንቀጽ 40

## የቀበሌ አስተዳደር አካላት

የቀበሌአስተዳደር የሚከተሉት አበይት አካላት ይኖሩታል፡-

1. የቀበሌ ምክር ቤት፤
2. የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤትና፤
3. የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት ናቸው፡፡

**አንቀጽ 41**

**የቀበሌ ምክር ቤት**

እያንዳንዱ የቀበሌ አስተዳደር እርከን የራሱምክርቤትየሚኖረውሲሆንተጠሪነቱለመረጠው ሕዝብናለታቀፈበት የወረዳአስተዳደር ምክር ቤት ነው፡፡

**አንቀጽ 42**

**የቀበሌ ምክር ቤት አባላት**

የቀበሌ ምክር ቤት አባላት፡-

1. በዚህ አዋጅ ክፍል አምስት ላይ በተመለከተው መሠረት በቀበሌ ነዋሪ ሕዝብ በቀጥታይመረጣሉ፤
2. የምክር ቤት አባላቱ ለመረጠው ሕዝብ ተጠያቂ ይሆናል፤
3. የምክር ቤት አባላት የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ነው፤
4. የምክር ቤቱን ስብሰባ የሚመሩና የሚያስተባብሩ አፈ-ጉባኤና ምክትል አፈ-ጉባኤ ከመካከላቸው በምርጫ ይሰየማሉ፤
5. በምክር ቤቱ ውስጥ ድምጽ የመስጠት መብት አላቸው፡፡

**አንቀጽ 43**

**የእጩነት መስፈርት**

በሀገሪቱ የምርጫ ሕግና በዚህ አዋጅ አንቀጽ 20 ላይ ስለወረዳ ምክር ቤት አባላት የተደነገገው መሥፈርት በቀበሌ ምክር ቤት አባላትም ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

**አንቀጽ 44**

**ድምጽ የማይሰጡ አባላት**

የቀበሌ ምክር ቤት በምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ የሚሳተፉ ነገር ግን ድምጽ የማይሰጡ ቀጥሎ የተመለከቱትን ሊያካትት ይችላል፡-

1. የቀበሌ ምክር ቤት አባላት ያልሆኑ የቀበሌ አስተዳደር አባላት፤
2. በቀበሌ ውስጥ የሚሠሩ የግብርና ልማት ፣ የጤና ኤክስቴንሽንና የትምህርት ባለሙያዎች፤

3. አፈ-ጉባኤው በስብሰባው ላይ እንዲሣተፉ የሚጋብዛቸው ሕዝባዊ ማህበራት አባላት፡፡

**አንቀጽ 45**

**የምክር ቤት አባላት ሥነ-ምግባር መመሪያ**

የቀበሌ ምክር ቤት አባላት የሥነ-ምግባርና የውስጥ አሠራር በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

**አንቀጽ 46**

**የአፈ-ጉባኤ ሥልጣንና ተግባር**

የቀበሌአፈ-ጉባኤ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የቀበሌውን ምክር ቤት ወቅታዊ ስብሰባ ይጠራል፣ ስብሰባውንም ይመራል፤
2. የምክር ቤቱን የመወያያ አጀንዳ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣ ስብሰባውንም በአጀንዳው መሠረት ይመራል፤
3. ቃለ-ጉባኤዎቹ በአግባቡ መያዛቸውንና መጠበቃቸውን ያረጋግጣል፤
4. ምክር ቤቱን በመወከል ከሶስተኛ ወገኖች ጋር ግንኙነት ያደርጋል፤
5. ምክር ቤቱ በአባላት ላይ የሚወስደውን የዲስፕሊን እርምጃዎች ያስፈፅማል፤
6. የምክር ቤቱ ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚቴዎችን ያስተባብራል፤
7. ከምክር ቤቱ የሚሠጡ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

**አንቀጽ 47**

**የምክትል አፈ-ጉባኤው ሥልጣንና ተግባር**

የቀበሌ ምክር ቤት ምክትል አፈ-ጉባኤ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. አፈ-ጉባኤው በማይኖርበት ወይም የተሠጠውን ተግባራት ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶ ይሠራል፤
2. በአፈ ጉባኤው ወይም በምክር ቤቱ ተለይቶ የሚሰጡ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## አንቀጽ 48

## ከቀበሌ ምክር ቤት አባልነት ስለማቋረጥ

የቀበሌ ምክር ቤት አባልነት በሚከተሉት ሁኔታዎች ሊቋረጥ ይችላል፡-

1. የምክር ቤቱ አባል በህገ-መንግሥቱ የተመለከቱትን የተመራጭነት ማረጋገጫ መስፈርቶች አለማሟላቱ ሲረጋገጥ፤
2. የምክር ቤቱ አባል የተመረጠበት ቀበሌ ለሁለት ሲከፈል ወይም ሲዋሃድ፤
3. የምክር ቤቱ አባል ከቀበሌው በላይ ለሆኑ ምክር ቤቶች ሲመረጥ፤
4. የምክር ቤቱ አባል ያለበቂ ምክንያት ለአራት ተከታታይ ጊዜያት ከምክር ቤቱ ስብሰባ ሲቀር፣ በቂ ምክንያት የሚለው እንደ ጊዜው ሁኔታ ተመዝኖ የሚወሰነው በምክር ቤቱ ይሆናል፤
5. የምክር ቤቱ አባል በሙስናና በሌሎች ወንጀሎች ከአንድ አመት በላይ ተፈርዶበት ከታሠረ፤
6. የምክር ቤቱ አባል በራሱ ፈቃድ አመልክቶ ሥልጣን ከለቀቀ፤
7. አግባብ ባለው ህግ መሠረት በመራጩ ህዝብ አመኔታ ሲያጣ
8. የምክር ቤቱ አባል በሞት ሲለይ ወይም ችሎታ ሲያጣ፤
9. ምክር ቤቱ በሚመለከተውና ሥልጣን ባለው አካል እንዲበተን ሲደረግ ነው፡፡

## አንቀጽ 49

## የቀበሌ ዋና አስተዳዳሪ

እያንዳንዱ ቀበሌ ለቀበሌው ምክር ቤትና ለወረዳ አስተዳደር ተጠሪ የሆነ አስተዳደር የሚኖረው ሲሆን፡-

1. የቀበሌው አስተዳደር በቀበሌው ምክር ቤት ውስጥ አብላጫ የምክር ቤቱ አባላት ባለው የፖለቲካ ድርጅት ወይም ድርጅቶች አቅራቢነት ከምክርቤቱ አባላት መካከል ተመርጦ ይሰየማል፤
2. የቀበሌው አስተዳደር የሥራ ዘመን ከቀበሌ ምክር ቤት የሥራ ዘመን ጋር እኩል ይሆናል፤
3. የቀበሌ አስተዳደሪ ከሥልጣኑ የሚነሣበት ሁኔታ ከምክር ቤቱ አባላት ዘመን ጋር እኩል ይሆናል፤

4. የቀበሌ አስተዳዳሪ ከሶስት ወር አስቀድሞ ለቀበሌው ምክር ቤት በጽሁፍ አሣውቆ ስልጣኑን በገዛ ፈቃዱ ሊለቅ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 50

## የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት አባላትና ተጠሪነት

ቀበሌው ተጠሪነቱ ለቀበሌው ምክር ቤትና ለቀበሌው ዋና አስተዳደሪ የሆነ የአስተዳደር ምክር ቤት ይኖረዋል፡፡

## አንቀጽ 51

## የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት አባላት

የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት አባላት ቁጥር የሥራውን ክብደትና ስፋት ከግምት በማስገባት የሚወሰን ሆኖ ቀጥሎ የተመለከቱትን ይጨምራል፡-

1. ዋና አስተዳዳሪ፤
2. ምክትል አስተዳዳሪ፤
3. እንዳግባብነቱ በዋና አስተዳዳሪው የሚታጭና በቀበሌ ምክር ቤት የሚፀድቅ፤
4. በዋና አስተዳዳሪው የሚታጩና በምክር ቤቱ የሚፀድቅ የአስተዳዳር ምክር ቤት አባላት ከቀበሌው ምክር ቤት፣ ከግብርና፣ ከጤናና ከትምህርት ባለሙያዎች ይሆናሉ፤
5. የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት ሹመት የወጣቶችንና የሴቶችን ተሳትፎ ያረጋገጠና ያካተተ፣ ጉዳተኞችን የሚያበረታታ መሆን አለበት፤
6. የአስተዳደር ምክር ቤት አባላት ከሚመረጡበት ሁኔታ ጋር ተመሣሣይ ይሆናል፤
7. የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት አባላት ኃላፊነት፣ ደመወዝና ዲስፐሊን የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፤
8. የአስተዳደር ምክር ቤት አባላት የሥራ ዘመን ከቀበሌ ምክር ቤት አባላት የሥራ ዘመን ጋር እኩል ይሆናል፤
9. የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት አባላት ከስልጣናቸው የሚነሱበት ሁኔታ ከቀበሌ ም/ቤት አባላት ስንብት ከወረዳው  አስተዳደር ምክር ቤት አባላት አንደ አግባብነቱ ተመሣሣይ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 52

## የቀበሌ ምክር ቤት ተግባርና ኃላፊነት

የቀበሌ ምክር ቤት በክልሉ ሕገ-መንግሥት እና በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የቀበሌውን ዋና አስተዳዳሪ ከመካከላቸው በመምረጥ ይሾማል፡፡ የቀበሌውን ምክትል አስተዳዳሪና የአስተዳደር ምክር ቤት አባላትን ሹመት ያፀድቃል፤
2. በዋና አስተዳሪው አቅራቢነት የማህበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞችን ሹመት ያፀድቃል፤
3. በበላይ የአስተዳዳር ርከኖች በየጊዜው የሚመጡትን መመሪያዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፤
4. ቀበሌውን የሚመለከቱ ጉዳዮች በታቀፈበት ወረዳ ወይም ሌላ አካል ስትራቴጂያዊ ወይም አመታዊ ዕቅድ ውስጥ መካተቱን ያረጋግጣል፤
5. ማህበረ-ሰቡ በልማት ዕቅድ ዝግጅት፣ በአፈፃፀምና ግምገማ ሂደት እንዲሳተፍ ያደርጋል፤
6. በወረዳው ዕቅድ ውስጥ አካባቢውን ወይም ቀበሌውን አስመልክቶ የተለዩትን ዕቅዶች ስንብት ጋርበቀበሌው ዕቅድ፣ ልዩ የልማት ፕሮጀክቶችና ተግባራት ውስጥ መካተታቸውን ያረጋግጣል፤
7. የቀበሌውን የልማት ዕቅድ ያፀድቃል፤
8. በአካባቢው ወይም በቀበሌው የሚከናወኑትን ዕቅዶችና ፕሮጀክቶች አፈፃፀም ያመቻቻል፤
9. የዕቀዶችንና የፕሮጀክቶችን አፈፃፀም ይከታተላል፣ ይገመግማልም፡፡ በአፈፃፀም የተገኙ ውጤቶችን መሠረት በማድረግ ከወረዳ አስተዳደር ጋር በመመካከር ተገቢውን ውሳኔ ይሰጣል፤
10. የአካባቢውን የተፈጥሮ ሃብት አስተዳደር ይከታታላል፣ ነዋሪው ሕዝብ አካባቢውን እንዲጠብቅና እንዲከባከብ ያደርጋል፤
11. በቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት አባላት እንዲሁም ምክር ቤቱ ባቋቋማቸው ማንኛውም ኮሚቴ መካከል የሚኖረውን የሥራ ክፍል ይወስናል፤
12. በአስተዳደር ምክር ቤት የቀረቡለትን የውሳኔ ሃሣብ በመመርመር ያፀድቃል፤

13. በቀበሌው ውስጥ ለልዩ ልዩ ዓላማ ማለትም ለምርጫ፣ ለዕቅድ ዝግጅት፣ ለመሠረተ-ልማት ግንባታ፣ ለአገልግሎት አሰጣጥና በማህበረ-ሰብ ተሳትፎ የተፈጠሩትን ወሰኖችና የማህበረ-ሰቡን ወሰኖች በመለየት ይመዘግባል፤
14. በዙሪያው ከሚገኙ ቀበሌዎች ጋር የሚፈጠረውን ወሰን አለመግባባት ይፈታል፣ በቀበሌ ደረጃ ሊፈቱ ያልቻሉትን ግጭቶች ለወረዳው ምክር ቤት ያሳውቃል፤
15. በቀበሌው ነዋሪዎች መካከል ከመሬት ባለቤትነት ጋር ተያይዘው የሚነሱ የወሰን ጉዳዮችን ይፈታል፤
16. ምክር ቤቱ የሚመራበትን የስነ-ምግባርና የውስጥ አሠራር መመሪያ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን እንዲወጣ ያደርጋል፣ ይተገብራልም፤
17. በቀበሌ ውስጥ ሰላም፣ ደህንነት፣ ሕግና ሥርዓት መጠበቁን ያረጋግጣል፤
18. ከቀበሌው ማህበራዊ ፍርድ ቤት የአፈፃፀም ሪፖርት ይቀበላል፣ አስተያየትም ይሰጣል፤
19. የቀበሌውን ነዋሪዎች እንደ አስፈላጊነቱ በነጠላም ሆነ በጉባኤ በመጥራት ልዩ ጠቃሜታ ባላቸው ጉዳዮች ላይ ያማክራል፤
20. የቀበሌ አስተዳደሪውንና የአስተዳደር ምክር ቤቱን እንዲሁም የሌሎች አስፈጻሚ አካላት የሥራ አፈፃፀም ይከታተላል፣ይገመግማልም፤
21. ኃላፊነቱን በሥሩ ለተቋቋሙት ኮሚቴዎች እንደ አስፈላጊነቱ ውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

## <u>አንቀጽ 53</u>

## <u>የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት ተግባራት</u>

የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፡-

1. በበላይ የአስተዳደር እርከኖች ፀድቀው የወጡትን ፖሊዎች፣ አዋጆች፣ ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ተግባራዊ ያደርጋል፤
2. የቀበሌውን ዓመታዊ ዕቅድ ያዘጋጃል፣ ለምክር ቤቱ በማቅረብም እንዲፀድቅ ያደርጋል፤
3. በበላይ አስተዳደር እርከኖች ስትራቴጂያዊ ዕቅድና ፖሊሲዎች ውስጥ የተካተቱትንና በቀበሌው ምክር ቤት የፀደቁትን የልማት ዕቅዶችና ፕሮግራሞች ተግባራዊ ያደርጋል፤
4. በቀበሌው ውስጥ የሚሰጡትን ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ አገልግሎት አቅርቦቶችን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራልም፤

5. በቀበሌው አስተዳደር አማካኝነት በየወቅቱ የሥራ ለቀበሌው ምክር ቤትና ለሚመለከተው የበላይ አካላት ያቀርባል፤
6. የቀበሌ ነዋሪዎችን ሰላምና ደህንነት ይጠብቃል፣ የቀበሌውን የፀጥታ አስከባሪ ኃይል ይመራል፣ የሥራ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፣ይቆጣጠራልም፤
7. የሕዝቡን ግንዛቤ በማሳደግ የገጠር ልማት እንዲፋጠን ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
8. የቀበሌውን የተፈጥሮ ሀብት በመጠበቅ በመንከባከብና ፍትሃዊ አጠቃቀምን በማረጋገጥ ዘላቂ ልማት እንዲሰፍን ያደርጋል፤
9. በቀበሌ ውስጥ የሚገኙ ቅርስና ውርስ ለአሁኑና ለመጪው ትውልድ የሚኖራቸውን ጠቀሜታ በመረዳት አስፈላጊውን ጥበቃና እንክብካቤ ያደርጋል፤
10. በቀበሌው ምክር ቤት፣ በወረዳ አስተዳደርና በሌሎች የበላይ አስተዳደር እርከኖች የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

## <u>አንቀጽ 54</u>

## <u>የቀበሌ ዋና አስተዳዳሪ ሥልጣንና ተግባር</u>

የቀበሌ አስተዳዳሪ የቀበሌ ዋና አስተዳዳሪ ሆኖ ቀጥሎ የተመለከቱት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. ቀበሌውን በመወከል በወዳረው ምክር ቤትና በሌሎች አስፈላጊ ስብሰባዎች ይሳተፋል፣ተገቢ ሆኖ ሲያገኝ በቀበሌው ስም አስተያየት ሊሰጥ ይችላል፤
2. የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት እጩ አባላትን ለምክር ቤቱ አቅርቦ ያስፀድቃል፤
3. የቀበሌውን ሕዝብ አስተያየት ከግንዛቤ በማስገባት እጩ የማህበራዊ ፍ/ቤት ዳኞችን ለቀበሌው ምክር ቤት በማቅረብ ያስፀድቃል፤
4. የምክትል አስተዳዳሪውንና የእያንዳንዱን የአሰተዳደር ምክር ቤት አባላት እንዲሁም የሚመሯቸውን ሴክተር መ/ቤቶች የሥራ አፈፃፀም ይከታተላል፣ ይቆጣጠራልም፤
5. የቀበሌውን አስተዳደር ምክር ቤት ስብሰባ ይጠራል፣ ስብሰባውንም ይመራል፤
6. በቀበሌው ምክር ቤት፣በወረዳ አስተዳደርና በሌሎች የበላይ አስተዳደር እርከኖች እንዲያስፈፀም የተሰጡትን ፖሊሲዎች፣አዋጆች፣ሕጎች፣ደንቦችና መመሪያዎች በቀበሌው አስተዳደር ውስጥ ትኩረት በመስጠት ተግባራዊ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤
7. የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት የሥራ አፈፃፀሙንለቀበሌው ነዋሪ ሕዝብና ለታቀፈበት ወረዳ ወይም ሌላ አካል ሪፖርት ያቀርባል፤

8. በቀበሌው ምክር ቤት የፀደቁት ዕቅዶች በአስተዳደር ምክር ቤት መተግበሩን ያረጋግጣል፤
9. በቀበሌው ሰላምና ሥርዓት መከበሩን ያረጋግጣል፤
10. በቀበሌው አስተዳደር ዕቅድና ሥራ አፈፃፀም ላይ ሕዝቡ ግልጽና ይፋ ውይይት እንዲያደርግበት ያደርጋል፤
11. በቀበሌው ምክር ቤት፣ በወረዳ አስተዳደርና በሌሎች የበላይ አስተዳዳር እርከኖች የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

## አንቀጽ 55

## የቀበሌ ምክትል አስተዳዳሪ ስልጣንና ተግባር

የቀበሌው ም/አስተዳዳሪው ተጠሪነቱ ለቀበሌ ዋና አስተዳደር ሆኖ ቀጥሎ የተመለከቱት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የቀበሌው አስተዳዳሪ በማይኖርበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜ ተክቶ ይሠራል፤
2. በቀበሌው ዋና አስተዳደሪና በቀበሌው ምክር ቤት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

## አንቀጽ 56

## የቀበሌ አስተዳደር ጽህፈት ቤት

የቀበሌ አስተዳደር የራሱ የሆነ ጽህፈት ቤት ይኖረዋል፡፡

## አንቀጽ 57

## ስለ ቀበሌ የሴክተር መህፈት ቤት ወኪሎች

በቀበሌው የተመደቡ የወረዳው ሴክተር መስሪያ ቤት ወኪሎች በቀበሌ ተመድበው የሚሠሩ የወረዳ ወይም የሌላ ሴክተር መስሪያ ቤት ኃላፊዎች ወይም ባለሙያዎች ማለትም የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራን፣የግብርና ልማትና የጤና ኤክስቴሽን ወዘተ…ሠራተኞች የሚያካትት ሆኖ፡-

1. በቀበሌው የየመስሪያ ቤቶቻቸውን ስትራጂክና ዓመታዊ ዕቅድ ይተገብራሉ፤

2. ከመስሪያ ቤቶቻቸው ጋር ተዛማጅ የሆኑ ሕጎች፣ደንቦች፣ መመሪያዎችና ደረጃዎች ተግባራዊ መደረጋቸውን ያረጋግጣሉ፤
3. ወሳኝና ልማት ነክ እስታስቲካዊ መረጃዎችን ለሴክተር መስሪያ ቤቶቻቸው አጠናቅረው ይይዛሉ፣ ለሚመለከተው አካልም መረጃውን ያስተላልፋሉ፤
4. ስርዓተ-ጾታና ኤች አይቪ ኤድስን የመከላከልና የመቆጣጠርን ተግባር በመደበኛ ተግባራቸው ውስጥ በማካተት ይተገብራሉ፤
5. በአካባቢው የሚገኘውን ሀብት በማንቀሳቀስ መደበኛና መደበኛ ያልሆነ ትምህርትና የግብርናና የጤና አገልግሎቶችን ይሰጣሉ፣ ያስፋፋሉም፤
6. ከወረዳው አስተዳደር ጋር በመሆን በተመደቡበት የሥራ መስክ ቀበሌውና ኗሪው ሕዝብ የጎላ ተሳትፎ እንዲኖረው ያደርጋሉ፤
7. የሲቪል ሰርቪስ ንዑስ ፕሮግራሞችን ይተገብራሉ፤
8. ወቅታዊ ሪፖርት ለመስሪያ ቤቶቻቸው፣ ለቀበሌ አሰተዳደርና በሕግ ለተፈቀደላቸው አካላት ያቀርባሉ፡፡

## አንቀጽ 58

## የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት

የቀበሌው አስተዳደር የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤቶች የሚኖሩት ሲሆን፡-

1. ማህበራዊ ፍርድ ቤቱ የቀበሌ የዳኝነት አካል ደረጃ ያለውና በሌላ ሕግ የተሰጣቸውን ጉዳይ ይመለከታል፤
2. የማህበራዊ የፍርድ ቤቱ ዳኛ በቀበሌው አስተዳዳሪ ከተመለመለና የህዝብ አስተየየት ተሰጥቶ ከታጨ በኂላ በቀበሌው ምክር ቤት ይሾማል፤
3. ማህበራዊ የፍርድ ቤቱ ዳኛ ሥራ ዘመን የቀበሌው ምክር ቤት የሥራ ዘመን ይሆናል፡፡

# ክፍል አራት

## የስብሰባው ሥነ -ሥርዓት

## አንቀጽ 59

## የወረዳ ምክር ቤት የስብስባ ሥነ-ሥርዓት ቀጥሎ የተመለከተው ይሆናል

የወረዳ ምክር ቤት የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ቀጥሎ የተመለከተው ይሆናል፡-

1. የወረዳ ምክር ቤት ስብሰባ በአመት ቢያንስ አራት ጊዜ ይደረጋል፤
2. የወረዳ ምክር ቤት ስበሰባ በአፈ-ጉባኤው ወይም እሱ በማይኖርበት ጊዜ በምክትል አፈ-ጉባኤው ይጠራል፣ ይመራል፤
3. ስብሰባው የሚካሄድበት ቦታና ጊዜ በምክር ቤቱ ይወሰናል፤
4. በምክር ቤቱና በአስተዳደር ምክር ቤቱ በምስጢር እንዲካሄድ ስምምነት ከተደረገባቸው ስብሰባዎች በስተቀር ለህዝብ ክፍት ይሆናሉ፤
5. የወረዳው ምክር ቤት ጽህፈት ቤት ኃላፊ በስብሰባው የሚኖር ሲሆን እርሱም የምክር ቤቱ ፀሐፊ እና ቃለ-ጉባኤዎችን እንዲያዝ ያደርጋል፤
6. አፈ-ጉባኤው የስብሰባ ቀን፣ቦታና አጀንዳ ከአምስት ቀናት በፊት ለምክር ቤቱ አባላት ያሣውቃል፤
7. ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በስብሰባው ላይ ከተገኙም ምልዓተ-ጉባኤ ይሆናል፣ የምክር ቤቱም ውሳኔ በስብስባው ላበተገኙት የምክር ቤቱ አባላት የአብላጫ ድምጽ ይወሰናል፤
8. የምክር ቤቱ አባላት የስብሰባ ቃለ-ጉባኤና ውሳኔዎች በአፈ-ጉባኤው ይረጋገጣሉ፣ የምክር ቤቱ አባላትም ቃለ-ጉባኤውን ያፀድቃሉ፤
9. ሌሎች ዝርዝር የስብሰባ ሥነ-ሥርዓቶችና የሥነ-ምግባር አሠራሮች በምክር ቤቱ በወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

## አንቀጽ 60

## የመስራች ጉባኤ

የወረዳና የቀበሌ ምክር ቤቶች የመስራች ጉባኤ በተሻሻለው የክልሉ ህገ መንግሥት አንቀጽ 94 (2) እና 105 (2) (ረ) መሠረት በዋና አስተዳዳሪው የሚጠራ ሲሆን የመስራች ጉባኤው፡-

1. አፈ-ጉባኤውንና ምክትል አፈ-ጉባኤውን ከመካከላቸው ይመርጣሉ፤
2. ዋና አስተዳዳሪውን ይመርጣሉ፤
3. የአስተዳደር ምክር ቤት አባላትን ይመርጣሉ፤
4. ቀጥሎ በተመለከተው ሁኔታ ቃለ-መሐላ ይፈጽማሉ፤
   ሀ) አፈ-ጉባኤውና ምክትል አፈ-ጉባኤው፣ ዋና አስተዳዳሪው፣ የአስተዳደር ምክር ቤት አባላት፣ በሙሉ በወረዳው ወይም ዳኛ አማካኝነት ቃለ-መሐላ ይፈጽማሉ፤

ለ) የቃለ-መሐላው ይዘትና የቃለ-መሐላው አሰጣጥ ስነ-ሥርአት “እኔ -----በዛሬው ዕለት የወረዳ ወይም የቀበሌ ምክር ቤት ወይም አመራር አባል ሆኜ ሥራዬን ስጀምር ለህገ-መንግስቱ ታማኝ በመሆን ከወረዳው ወይም ከቀበሌው እና ከሕዝብ የተጣለብኝን ኃላፊነት በቅንነት፣ በታማኝነት እንዲሁም ህግንና አሠራርን መሰረት በማድረግ ሥራዬን እንደምፈጽም ቃል እገባለሁ” የሚል ይሆናል፤

ሐ)ቃለ-መሐላ ከመፈፀሙ በፊት ማንኛውም አባል ሥራ አይጀምርም፤

መ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 (ሐ) የተገፀው ቢኖርም ከአቅም በላይ በሆነ አሳማኝ ሁኔታ መሀላ ያልፈፀመ ተሿሚ በአካባቢ አስተዳደር በሚገኘው ፍርድ ቤት ፐሬዚዳንት ወይም ዳኛ ወይም በህግና አስተዳደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ቀርቦ ቃለ መሀላ መፈፀም አለበት፡፡

## አንቀጽ 61

## የቀበሌ ወይም የወረዳ ምክር ቤቱ አስቸኳይ ስብሰባ

1. አፈ-ጉባኤው ከአንድ ሶስተኛ (1/3ኛ) በላይ የሚሆኑ የምክር ቤት አባላት ወይም በአስተዳደር ምክር ቤቱ ጠያቂነት ለአንድ ለተለየ ጉዳይ አስቸኳይ ስብሰባ ይጠራል፤ ጥያቄው በጽሁፍ መቅረብ አለበት፣
2. ስብሰባው ጥያቄው በቀረበ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ መጠራት አለበት፡፡

## አንቀጽ 62

## የወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት ስብሰባዎች

የወረዳ አስተዳደደር ምክር ቤት ወይም ካቢኔ ስብሰባዎች ቀጥሎ በተመለከተው ሁኔታ ይከናወናሉ፡-

1. የወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት ወይም ካቢኔ ቢያንስ በሳምንት አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያካሂዳል፡፡
2. የወረዳው ዋና አስተዳዳሪ በሚሰጠው መመሪያ መሰረት የጽ/ቤቱ ኃላፊ ስብሰባውን ይጠራል፡፡
3. የወረዳው ዋና አስተዳዳሪ እስከ አንድ ወር ድረስ ስብሰባውን መጥራት ካልቻለ 1/3ኛ የሚሆነው የመስተዳድር ምክር ቤት አባላት በአስተዳዳሪው ምትክ የጽ/ቤት ኃላፊ ስብሰባውን እንዲጠራ በጽሁፍ ሊጠይቁት ይችላሉ፡፡

4. የወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት ስብሰባ በዋና አስተዳዳሪው ወይም በምክትል አስተዳዳሪው ወይም ውክልና በተሰጠው የምክር ቤቱ አባል ሊመራ ይችላል፡፡
5. ከግማሽ በላይ የሚሆኑት የምክር ቤቱ አባላት በስብሰባው ላይ ከተገኙ ምልዓተ- ጉባኤው እንደተሟላ ይቆጠራል፡
6. የአስተዳደር ምክር ቤቱ ውሳኔዎችና ቃለ-ጉባኤዎች በዋና አስተዳዳሪው ይረጋገጣል፣
7. ሌሎች ምክር ቤቱ የሚመራባቸው የውስጥ አሰራሮች በምክር ቤቱ ይወሰናሉ፡፡

## አንቀጽ 63

## ሀብት ስለመመዝገብ

የወረዳ አስተዳደር ምክር ቤት አባላት በሙሉ ሥራ ከመጀመራቸው በፊት አግባብነት ካለው ሕጋዊ አካል ፊት ቀርበው ሀብታቸውን ያስመዘግባሉ፡፡

## አንቀጽ 64

## የፋይናንስ ጥቅምን ስለማሣወቅ

ማንኛውም የአስተዳደር ምክር ቤት አባል ከፋይናንስ ጋር የተያያዘ ጥቅም ወይም የራሱ/የራሷ ወይም ወይም የቤተሰቡ/የቤተሰቧ የምክር ቤት ወይም በአስተዳደር ምክር ቤት ውስጥ ውይይት በሚደረግበት ጉዳይ ወይም ኮንትራት ላይ የተለየ ጥቅም ያላቸው መሆኑን የመግለጽ ግዴታ አለበት፤ በመሆኑም በስብሰባው ላይ መሣተፍ ወይም በጉዳዩ ላይ ድምጽ መስጠት አይችልም፤በዚህ ጉዳይ ላይ የምክር ቤቱ አባላት በሚያደርጉት ስብሰባ ላይ ሊሣተፍ አይችልም፡፡

## አንቀጽ 65

## የቀበሌ ምክር ቤት ስብሰባዎች

የቀበሌ ምክር ቤት ስብሰባዎች ቀጥሎ በተመለከተው ሁኔታ ይካሄዳሉ፡-

1. መደበኛ ስብሰባዎች በወር አንድ ጊዜ ይከናወናሉ፣
2. ከግማሽ በላይ የምክር ቤት አባላት በስብሰባው ላይ ከተገኙ ምልአተ-ጉባኤው እንደተሟላ ይቆጠራል፣
3. ምክር ቤቱ የስብሰባውን ሂደት ቃለ-ጉባኤ በትክክል መያዙን ያረጋግጣል፣

4. ምክር ቤቱ የሚያደርጋቸውን ሌሎች ስብሰባዎችን በተመለከተ የራሱን የስብሰባ ሥነ-ስርዓት ሊያወጣ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 66

## የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት ስብሰባዎች

የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት ስብሰባዎች በሚከተለው ሁኔታ ይከናወናሉ፡-

1. የቀበሌ ዋና አስተዳዳሪ በሣምንት አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ይጠራል፤
2. የአስተዳደር ምክር ቤቱ የሚያደርጋቸው ስብሰባዎች በዋና አስተዳዳሪው ወይም በምክትል አስተዳዳሪው ወይም ውክልና በተሰጠው የምክር ቤቱ አባል ሊመራ ይችላል፤
3. ከግማሽ በላይ የሆኑ የምክር ቤቱ አባላት ከተገኙ የስብሰባው ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፤
4. የአስተዳደር ምክር ቤቱን ውሣኔዎችና ቃለ-ጉባኤ ዋና አስተዳዳሪው ያረጋግጣል፤
5. ሌሎች መስሪያ ቤቱ የሚመራባቸው የውጥ አሠራሮች በምክር ቤቱ ይወሰናሉ፡፡

## አንቀጽ 67

## ውሳኔዎች

1. የወረዳና የቀበሌ ምክር ቤት ውሳኔዎች በስብሰባው ላይ በተገኙ አባላት በአብላጫ ድምጽ ይወሰናል፣ ድምጽ እኩል በተከፈለ ጊዜ ሰብሳቢው ወሣኝ ድምጽ ይኖረዋል፡፡
2. የወረዳና የቀበሌ አስተዳደር ምክር ቤት አባላት ለሚያሳልፏቸው ውሣኔዎችና ለሚወስዷቸው እርምጃዎች የግልና የጋራ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

## *ክፍል አምስት*

## ምርጫ

## አንቀጽ 68

## የምርጫ አፈፃፀም

የወረዳና የቀበሌ ምክር ቤት አባላት መደበኛና የማሟያ ምርጫ የሚካሄደው በምርጫ ህግና የምርጫ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ይከናወናሉ፡፡

## አንቀጽ 69

## የተለየ ውክልና የሚሰጣቸው ቡድኖች

ምርጫ የሚከናወነው በፖለቲካ ፓርቲዎች ደረጃ ቢሆንም የግል ተወዳዳሪዎችም መወዳደር ይችላሉ፤ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሰፊ የውክልና መሠረት እንዲኖራቸው ተወዳዳሪዎቻቸው ከተለያዩ ብሄረሰቦች፣ ቡድኖች፣ ታዋቂ ግለሰቦች፣ ሴቶች፣ አርሶ አደሮች፣ ወጣቶች፣ ምሁራን፣ ነጋዴዎች፣ አካል ጉዳተኞችና ትኩረት ካልተሰጣቸው የሕብረተሰብ ክፍሎች እጩዎችን የማቅረብ ኃላፊነት አለባቸው።

## አንቀጽ 70

## የወረዳ ምርጫ

ከላይ በአንቀጽ 69 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ለወረዳ ምክር ቤት አባልነት የሚመረጡት የቀበሌ ነዋሪ ሆነው በሚከተለው ሁኔታ ይሆናል፦

1. እያንዳንዱ ቀበሌ እንደምርጫ ክልል ይቆጠራል፤
2. ከእያንዳንዱ ቀበሌ የሚመረጠው የምክር ቤትአባል ቁጥር የሚወሰነው በሕዝቡ ቁጥርና በምርጫ ሕግ ላይ በተጠቀሰው መሠረት ይሆናል፤
3. የእያንዳዱ የምርጫ ቀበሌ ወሰን በምርጫ ቦርድ ይወሰናል።

## አንቀጽ 71

## የቀበሌ ምርጫ

1. የቀበሌ ምክር ቤት አባላት በምርጫ ህጉ መሠረት ከቀበሌ ነዋሪ ህዝብ መካከል ይመረጣል።
2. የቀበሌ ምክር ቤት አባላት ቁጥር የሚወሰነው በቀሌው ውስጥ እንደየጉጦቹ ስፋት የህዝብ ቁጥር ብዛት በምርጫ ቦርድ በሚወሰነው ይሆናል።
3. የጉጦቹ የምርጫ ድንበር የሚወሰነው በቀበሌው አስተዳደርና በምርጫ ቦርድ ይሆናል።

## *ክፍል ስድስት*

## የአከባቢ አስተዳደር ስልጣንና ተግባር

### አንቀጽ 72

### የወረዳ አካባቢ አስተዳደር ስልጣንና ተግባር

የተሻሻለው የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ህገ-መንግስትድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የወረዳ አካባቢ አስተዳዳር ክልል ውስጥ፡-

1. ሕግ አውጪ፣ሕግ አስፈፃሚና የዳኝነት ስልጣን ይኖረዋል፤
2. የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ህገ-መንግስትና ሌሎች ሕጐችን ይጠብቃል፤ ሰላም ፣ደህንነትና ዲሞክራሲያዊ አስተዳደር እንዲሰፍን ያደርጋል፤
3. በፌደራልና በክልል መንግስታዊ አካላት የወጡትን ፖሊሲዎች፣ሕጐችና መመሪያዎች ይፈጽማል፤
4. በህግ በተሰጠው ሥልጣን የራሱን መመሪያዎችና የውስጥ መመሪያዎች ሥርዓቶች ያወጣል፡፡ ዝርዝር ስልጣንና ተግባር በክልሉ ሕገ-መንግስትና አካባቢ አስተዳደር ሴክተር መሥሪያ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ የሚወሰን ይሆናል፤
5. በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መንግስት የመሬት አስተዳደር አዋጅ መሠረት የመሬት አስተዳደርና ሌሎች የተፈጥሮ ኃብቶች ዘላቂ የሆነ ጥበቃ እንዲደረግ ይቆጣጠራል፣ ድጋፍም ይሰጣል፤
6. ስትራቴጂያዊና ወቅታዊ ዕቅዶችን በማዘጋጀት ዘላልማት እውን አንዲሆን ያመቻቻል፤
7. በህብረተሰቡ ኃብትና ፍላጐቶች ላይ የተመሠረቱ ውጤታማና ወጪ ቆጣቢ የሆኑ አገልግሎቶችን ይሰጣል፤
8. በዚህ አዋጅ ላይ በተገለፀው መሠረት በሰው ኃይልና በፋይናንስ ላይ የማዘዝ ሥልጣን ይኖረዋል፤
9. የተሰጠውን ተግባርና አገልግሎት ለቀበሌዎች ወይም በተለየ ሁኔታ ለሌሎች የአስተዳደር እርከኖች በውክልና የመስጠት ወይም መልሶ የመውሰድ ስልጣን ይኖረዋል፤ ይህ የሚሆነው፡-

ሀ) ሁለቱ ወገኖች ስምምነት ሲኖራቸው፤

ለ) በውክለና የተሰጣቸውን ተግባራት፣ ስልጣንና አገልግሎቶች ለማከናወን የሚያስችል አስፈላጊ ኃብት ሲመደብ፤

ሐ) ትክክለኛ የሆነ የክትትልና የሱፐርቪዥን አሰራር ስርዓት ሲዘረጋና ሥራ ላይ ሲውል፤

መ) በአካባቢው የሚፈለገውን ውጤት እውን ለማድረግ በውክልና መሠረት የአካባቢው ሕዝብ ትኩረት ማግኘት ሲችል ነው፡፡

## አንቀጽ 73

## የቀበሌ አካባቢ አስተዳደር ሥልጣንና ተግባር

በክልሉ ህገ-መንግስት በቀበሌ አስተዳደር የተሰጠው ስልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ የቀበሌ አስተዳደሩ በአስተዳደሩ ክልል ውስጥ፡-

1. በክልሉ ህገ-መንግስትና በበላይ የአስተዳደር እርከኖች የወጡትን ህጐች ይጠብቃል፡፡ ሰላም፣ ደህንነትና ዲሞክራሲያዊ አሠራር እንዲሰፍን ያደርጋል፡፡
2. በወረዳው የአስተዳደር አካል የወጡትን መመሪያዎችንና ዕቅዶችን ይፈጽማል፡፡
3. የቀበሌ አስተዳደር በክልል መንግስት ከወጡ ህጐች ጋር በተጣጣመ መልኩ የራሱን የውስጥ አሰራር ሥርዓትን ያወጣል፣ ተግባራዊ መሆኑንም ያረጋግጣል፡፡
4. በበላይ የአስተዳደር እርከኖች የወጡትን ስትራቴጂዎችናዕቅዶች ከግምት ውስጥ በማስገባት የልማት ዕቅዶችን ያዘጋጃል፡፡ ማህበረሰቡን፣ ህዝባዊ ማህበራትን፣ የልማት ሠራተኞችንና ሌሎች በአካባቢው ልማት ላይ የሚሰሩ አካላትን ለማሣተፍ አፈፃፀማቸውን ይከታተላል፣ ይገመግማልም፡፡
5. በክልሉና በወረዳው የቴክኒክ ድጋፍ በመታገዝም ሆነ በራሱ ከአካባቢው እንክብካቤና ጥበቃ አንፃር የመሬት አጠቃቀም ዕቅድን ማዘጋጀትና እምቅ የልማት ኃይል ለማልማት በሚደረገው ጥረት ይሳተፋል፣ ያሳትፋልም፡፡
6. ከክልሉ መሬት አስተዳደር አዋጅ ጋር በተጣጣመ ሁኔታ በወረዳ አስተዳደር በውክልና የተሰጣቸውን የመሬት አስተዳደር ሥራዎችን ያከናውናል፡፡

7. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 72ንዑስ አንቀጽ9 ሥር በወረዳ አስተዳደር በውክልና የተሰጣቸውን ሥራዎች በቅልጥፍናና አሣታፊ በሆነ ሁኔታ ያከናውናል፡፡
8. የቀበሌውን ነዋሪ ሕዝብ ለአካባቢው ዕድገት በሚደረጉ የልማት ጥረቶችና በተፈጥሮ ኃብት ጥበቃ ላይ ያሳትፋል፣

## አንቀጽ 74

## የአካባቢ አስተዳደር የማቀድ ተግባራት

የአካባቢ አስተዳደር ዕቅድ በማቀድ በኩል የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል፡-

1. የአካባቢ አስተዳደሩን ዕድገት ለማፋጠን ጥረት ያደርጋል፡፡
2. የአካባቢ አስተዳደሩን የ5 ዓመት የስትራቴጂክ ዕቅድ ያዘጋጃል፡፡
3. ለአካባቢ አስተዳደር ተንከባላይ የፋይናንስ፣ ዓመታዊ የልማትና ሌሎች እቅዶችን ያዘጋጃል፡፡
4. በአካባቢ አስተዳደር ውስጥ የልማት ዕቅድንና የፖሊሲዎች አፈፃፀም ይከታተላል፡፤
5. በዚህ አዋጅ ወይንም በማናቸውም ሌላ ሕግ ከልማት ተግባራት ጋር ተያይዘው የተሰጡ ማናቸውንም ሥራዎችን ያከናውናል፡፡

## አንቀጽ 75

## ስለ ዕቅድና ታሳቢዎች

የመካከለኛ ጊዜ የልማት ስትራቴጂያዊ ዕቅድ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 74 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የወረዳ የአካባቢ አስተዳደር፡-

1. የአካባቢ ወቅታዊና ማህበራዊ፣ አካባቢያዊ፣ ባህላዊና ሥነ-ህዝባዊ ገጽታዎችንበማጥናት፤ እነዚህን ገጽታዎችንና አዝማሚያዎችን በመተንበይ እና ችግሮችን፣ እድሎችንና ፍላጐቶችን በመተንተንና በዚሁ ላይ በመመሥረት የአምስት (5) ዓመት ስትራቴጂያዊ ዕቅድ ያዘጋጃል፤ የሚዘጋጀው እቅድም፡-
   ሀ) የፌዴራልና የክልል ስትራቴጂያዊ የልማት ዕቅዶችንና ፓሊሲዎችን፤
   ለ) የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ቢሮና የሌሎች ሴክተር መ/ቤቶች ፖሊሲዎችንና መግለጫዎችን፤

ሐ) በታችኛው የአካባቢ አስተዳደር ውስጥ የሚገኙትን የቀበሌና የገጠር ከተሞችን የልማት ዕቅድና፤

መ) ከአካባቢው አስተዳደር ልማት ጋር የተገናኘ ማንኛውንም አግባብነት ያላቸውን ዕቅዶችንና ፖሊሲዎችከግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት፤

2. ስትራቴጂያዊ ዕቅድ የአካባቢ አስተዳደር በሚወስነው መሠረት፦

ሀ) የአካባቢውን ቀጣይ እድገት የሚያረጋግጥ ሰፊ ስትራቴጂያዊ አላማዎችና ግቦችን፤

ለ) በጥናት ወቅት ተለይተው በተቀመጡ ዓላማዎችንና ግቦች የሚያሣኩ በተከታታይ የወጡ ፖሊሲዎችንና ኘሮግራሞችን ማካተት አለበት።

3. የአካባቢው አስተዳደር ስትራቴጂያዊ የልማት ዕቅድ ዝግጅት ሂደት አሳታፊመሆን አለበት፤ ሂደቱም፦

ሀ) የታችኛው የአስተዳደር ተወካዮችን፤

ለ) የምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴዎች፤

ሐ) ሕዝባዊ ድርጅቶችን፤

መ) የልማት ኮሚቴዎችንና አግባብ ያላቸውን የልማት ድርጅቶች፤

ሠ) መንግስታዊ መዋቅሮችንና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ማሣተፍ አለበት።

4. የአካባቢ አስተዳደር ፖሊሲዎችና መርሃ ግብሮች ሲዘጋጅ፦

ሀ) በልማት ወደኋላ የቀሩ አካባቢዎችንና ለችግር የተጋለጡ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ለመደገፍ የሚያስችል ፍትኃዊነትን የሚያራምድ ልማት፤

ለ) የኢኮኖሚና የመሠረተ-ልማት ፍላጎቶች፤

ሐ) ቀጣይነት ያለው የአካባቢው ኃብቶች አጠቃቀም፤

መ) ምርታማነትን የሚያሣድግና ወጪ ቆጣቢ የሆኑ ተግባራት፤

ሠ) የአካባቢውን የሰው ሃይልና እውቀት በመጠቀም ለሴቶች፣ ለወጣቶችና በኣካል ጉዳተኞች ላይ ልዩ ትኩረት በመስጠት ላይ ያተኮረ ልማት፤

ረ) የህብረተሰቡን አቅም የሚገነቡና ያሳታፊነት ባህሪ ያላቸው ተግባራት፤

ሰ) በቀዳሚነት የልማት አፈፃፀም ግምገማ መሰረት ጠቃሚ የሆኑ ተሞክሮዎችን በመቀመርና ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ተግባራትን በመለየት አቅጣጫን በማስቀመጥ መሆን አለበት።

5. ረቂቅ ስትራቴጂያዊ የልማት ዕቅድ ለህዝቡ እንዲያቀርቡ በማድረግ ምክክርና ውይይት መደረግ አለበት፤ ከውይይቱ ከሚገኙአስተያየቶች መሰረት ሊሻሻልና ሊዳብር ይችላል፤
6. የአካባቢ አስተዳደር ምክር ቤት የህዝቡን ውይይት ተከታትሎ በረቂቅ ስትራቴጂያዊ የልማት ዕቅድ ላይ በመወያየትና የተደረጉ ማሻሻያዎችንና ለውጣቸውን ተቀብሎ የማስተናገድ ኃላፊነት አለበት፡፡
7. የአካባቢ አስተዳደር ምክር ቤት ከአካባቢው አስተዳደር የአስተደደር ምክር ቤት የቀረበለትን ረቂቅ ስትራቴጂያዊ ዕቅድ በመመርመርና በመወያየት ማሻሻያዎችንና ለውጦችን በማድረግ ያፀድቃል፡፡
8. የአካባቢ አስተዳደር የሥራ ኃላፊዎችና የበታች ሠራተኞች በፀደቀው ስትራቴጂያዊ ዕቅድ ላይ ሰፊ የግንዛቤ ማስጨበጫ ውይይት በማድረግ በዕቅዱ ላይ የባለቤትነትና የኃላፊነት ስሜት ማዳበር አለባቸው፡፡
9. በስትራቴጂያዊ ዕቅዱ ተግባራዊነት ላይ ምክር ቤቱ የሚወስናቸው ባለድርሻዎች በሚሳተፉበት አመታዊ ዕቅድ አፈፃፀም ግምገማና ክትትል ይደረግበታል፤ የታዩ ጠንካራና ደካማ ጐኖች ተለይተው በሪፖርት ከቀረቡ በኋላ በቀጣዩ አፈፃፀም ላይ ማስተካከያና አቅጣጫ ይቀመጥለታል፡፡

## <u>አንቀጽ 76</u>

## <u>የወረዳ አካባቢ አስተዳደር ዓመታዊ የልማት ዕቅድ ዝግጅት</u>

1. የአከባቢው አስተዳደር ዓመታዊ ዕቅድ ያዘጋጃል፤ ይህም በአመቱ የበጀት ዕቅድ ውስጥ መካተት አለበት፤ ይህ በሚደረግበት ጊዜ የአከባቢ አስተዳደሩ፡-
   ሀ) የእስትራቴጃዊ የልማት ዕቅዳቸውን ሃሳብና የአከባቢውን ዕድገት በሚመለከት የማንኛውንም የበላይ አካል ዕቅድ ሃሳብ መቀበል አለበት፤
   ለ) የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮና የሴክተር ቢሮዎች ፖሊሲዎችንና መግለጫዎችን ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባት አለበት፤
   ሐ) የበታች መዋቅሮችና የከተማዎች የልማት ዕድገት ትኩረት መሰጠት አለበት፤
   መ) የአከባቢውን ዕድገት የሚመለከቱ ማናቸውንም ተመሣሣይ ዕቅዶችንና ፖሊሲዎችን ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባት አለበት::

2. የአካባቢ አስተዳደር የአስተዳደር ምክር ቤቱ የቀረበው ዕቅድ ከአካባቢው አስተዳደር የሃብት አቅም ጋር የሚጣጣም መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፤ ይህንንም ለመፈፀም ለመጪው አመት የሚያዘው የሀብት ግምት ለማስፋት ጥረት በማድረግ:-

   ሀ)የአካባቢ አስተዳደሩን የሰው ሀይል፣ የራሱን ገቢ፣ በሕዝቡ ጉልበት የሚሠሩትን በመተመንና ሌሎች ሀብቶችን፤

   ለ) ከክልሉ መንግስት የሚገኝ የገንዘብ ድጐማ፤

   ሐ) ከሴክተር መሀፈት ቤቶች የሚገኝ የገንዘብ፣ የቁሳቁስና የባለሙያ ድጋፍ፤

   መ) ከመንግስት ወይም መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች የሚሰጥ ዕርዳታ ግምት ውስጥ በማስገባት መሆን አለበት::

3. የአካባቢ አስተዳደር ዓመታዊ ዕቅድ ዝግጅት ሂደት አሳታፊና የባለድርሻዎችን አስተዋጽኦ ያካተተ መሆን አለበት፡፡ በተለይም፡-

   ሀ)ዕቅዱ የተወሰኑ አካባቢዎችን በሚመለከት በሚሆንበት ጊዜጉዳዩ የሚመለከታቸውን ቀበሌዎችና ህዝቦችን ማማከር አለበት፤

   ለ)በሕብረተሰቡ አዳዲስ አገልግሎቶችን ለመስራት በሚታሰብበት ጊዜ የምክክር ጉባኤ መደረግ አለበት፡፡

4. ረቂቅ ዕቅዱ ለሕዝብ አስተያየት ሊቀርብና በሚሰጥ አስተያየት መሠረት ሊሻሻል ይችላል፡፡

5. የአስተዳደር ምክር ቤቱ በቀረበለት ረቂቅ ዕቅድ ላይ በመወያየት የተሰጡ ማሻሻያዎችንና ለውጦችን በመመርመር ያፀድቃል፡፡

6. ረቂቅ ዕቅዱ ለአካባቢ አስተዳደር ቀርቦ ከመጽደቁ በፊት ለሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ ተመርቶ ምርመራ ከተደረገ በኋላ ለምክር ቤቱ ቀርቦ ይፀድቃል፡፡

7. በፀደቀው ዓመታዊ ዕቅድ ላይ የአካባቢው አስተዳደር አመራር አካላትና የበታች ሠራተኞች በመወያየት የባለቤትነትንና የኃላፊነት ስሜት ማዳበር አለባቸው፡፡

8. የአካባቢውን አስተዳደር አመታዊ ዕቅድ መደበኛ ክትትልና ወቅታዊ የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ ይደረግበታል፡፡ ግምገማውም የበታች አስተዳዳር አካላትን /ቀበሌዎችን፣ሕዝባዊ ድርጅቶችን፣ የልማትኮሚቴዎችንና የማህበረሰብ ድርጅቶችን/ ያሳተፈ መሆን አለበት፡፡

## አንቀጽ 77

## የፕሮጀክትና የፕሮግራም አተገባበር

1. የወረዳ አካባቢ አስተዳደር የመስተዳደሩ ምክር ቤት ከዓመታዊ ዕቅዱ የመነጩ የፕሮጀክትና የፕሮግራም ዕቅዶች መከናወናቸውን ያረጋግጣል፡፡
2. የፕሮጀክት ኃሣቦች ሁሉ አዋጪነታቸው በጥናት የተደገፈና አጠቃላይ ወጪያቸውና የሚያስገኘው ጠቀሜታ ግምት የሚያሣይ ሆኖ፣ በተጨማሪም፡-

   ሀ) ገቢ የሚያስገኝና የሥራ ዕቅድየመፍጠር አቅሙ፤

   ለ) በግብርናና በኢኮኖሚ ዕድገት ላይ የሚኖረው አዎንታዊ ተፅዕኖወይም ፋይዳ፤

   ሐ) የአከባቢውን አቅም በመገንባት ረገድ የሚኖረው አቅም፣ ኃይል፣ አካባቢያዊ ክህሎትና ሀብት የመጠቀም፤

   መ) በአካባቢ ጥበቃ ላይ የሚያመጣው ተፅዕኖ፤

   ሠ) የሴቶችና የሕፃናት ኑሮ የመደገፍ አቅምና በማህበራዊ ኑሮ ላይ የሚያመጣው ፋይዳ እና፤

   ረ) ተከታታይነት ያለው ዕድገት ለማስገኘት ያለው አቅም ናቸው፡፡
3. የአካባቢ አስተዳደር ፕሮጀክቶች አፈፃፀም አስተዳደር፣

   ሀ) አሳታፊ በሆነ ሁኔታ የመተግበር፣ ተሳትፎን ማረጋገጥ፤

   ለ) የአካባቢውን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፤

   ሐ) ከልማት አጋሮች፣ ከመንግስት ሴክተር መስሪያ ቤቶችና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች እንዲሁም ከአካባቢው ሕብረተ-ሰብ ጋር ተገቢ የሆነ የትብብር ስርዓት መኖሩን ማረጋገጥ አለበት::
4. በአካባቢ አስተዳደር ውስጥ በማንኛውም አካል የሚሰሩ ፕሮጀክቶች የአካባቢ አስተዳደሩ የአስተዳደር ምክር ቤት ከሌሎች ባለድርሻዎች ጋር በመሆን ባፀደቀውና ሥራ ላይ በዋለው አሠራር መመሪያ መሠረት ክትትልና ግምገማ ይደረግባቸዋል፣

5. የሁሉም የመሠረተ-ልማት ኘሮጀክቶች ዕቅዶች በሚዘጋጅበት ጊዜ የወረዳው የአስተዳደሩ ምክር ቤት በሚያወጣው መስፈርት መሠረት የጥገና ዕቅዳቸውም አብሮ ተካቶ መቅረብ አለበት፡፡

## አንቀጽ 78

## የቴክኒክ ዕቅድ ኮሚቴ

1. በሚመለከተው እስታፍ የሚደገፍ የወረዳው የቴክኒክ ዕቅድ ኮሚቴ በወረዳው ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽህፈት ቤት ይቋቋማል፡፡
2. የቴክኒክ ዕቅድ ኮሚቴ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፡-

   ሀ) ለማንኛውም የዕቅድ ዝግጅት የቴክኒክ ድጋፍና ምክር ይሰጣል፤

   ለ) የስትራቴጂክ ዕቅድ ዝግጅቶችን ያስተባብራል፤

   ሐ) ረቂቅ ዓመታዊ ዕቅድ ሰነድ ያዘጋጃል፤

   መ) የምክር አገልግሎት ሒደትን ይመራል፤

   ሠ) የክትትልና የግምገማ ሂደትን ይመራል፤

   ረ) የዕቅድ መረጃ ሥርዓት ይመሠርታል፤

   ሰ) የታቀዱ ሥራዎችን ቴክኒካዊ አፈፃፀም ይከታተላል፡፡

3. የወረዳው አስተዳደር ምክር ቤት የቴክኒክ ዕቅድ ኮሚቴን ሥራ ለመደገፍ የምክር አገልግሎት የሚሰጥ አካል እንዲቀጠር ሊያዝ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 79

## አገልግሎት አሰጣጥ

የወረዳ አካባቢ አስተዳደሮች ቀጥሎ በተመለከተው ሁኔታ አገልግሎት የመስጠት ኃላፊነት አለባቸው፡-

1. ይህ አዋጅና ሌሎች ማናቸውም ሕጐች እንደተጠበቁ ሆነው የወረዳ አካባቢ አስተዳደሮች መስሪያ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ በተሰጣቸው ስልጣንና ተግባር መሠረት ማናቸውንም ተግባራት የማከናወንና አገልግሎቶችን የመስጠት ኃላፊነት አለባቸው፤
2. በአንድ ሴክተር መህፈት ቤት ውስጥ በጋራ ወይም በፌደራልና በክልል የሚሰጡ አገልግሎቶችን ለሚመለከተው የወረዳ አካባቢ አስተዳደር የተጠቀሰውን አገልግሎት

ለመስጠት የሚያስችለው የትብብር ስልቶችን በመቀየስ፣ አገልግሎቱ የወረዳ አካባቢ አስተዳደሩ ካፀደቀው የልማት ዕቅድ ጋር ተጣጥሞና ተቀናጅቶ መሠጠቱን ማረጋገጥ፤

## አንቀጽ 80

## የተፈጥሮ ኃብትና የመሬት አስተዳደር

የወረዳ አስተዳደሮች የተፈጥሮ ኃብትን በማስተዳደር ረገድ የሚከተሉት ኃላፊነቶች ተጥሎባቸዋል፡-

1. በክልሉ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ መሠረት የወረዳውን የመሬት አያያዝና አጠቃቀምን ይመራል፤
2. የወረዳው አስተዳደር የአካባቢውን የተፈጥሮ ሀብት በሚከተሉት ሁኔታ ይጠብቃል፡-

   ሀ) ከክልሉ የአካባቢ ጥበቃ፣ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም መስሪያቤቶች ፖሊሲ ጋር የሚጣጣሙ ስትራቴጂዎችና ፖሊሲዎችበስትራቴጂያዊና ዓመታዊ ዕቅድ ውስጥ በማካተት፤

   ለ)የተፈጥሮ ሃብትን የሚጐዳ አጠቃቀም ለመከላከልና የአካባቢውን አየር፣ ውሃ፣ አፈርና የአካባቢውን ንፅህና የሚበክል ድርጊቶችና ተግባራት የሚከላከል የአሠራር ስልት ይቀይሣል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡
3. የወረዳና የቀበሌ አስተዳደሮች በጋራ በመሆን የመሬት ይዞታዎች የሚመዘግበውና ሰርተፊኬት የሚሰጠውን የባለስልጣን መሥሪያ ቤት ቅርንጫፍን በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፡፡
4. የወረዳው አስተዳደር የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ በሚያዘጋጅበት ጊዜ ቀበሌዎችን ማማከርና ስትራቴጂያዊ ግንዛቤ ማስጨበጥ አለበት፤ እነዚህም፡-

   ሀ)ከተፈጥሮ ሥነ-ምህዳር፣ በመሬት አጠባበቅና ከሌሎች የተፈጥሮ ኃብቶች ጋር በተጣጣመ ሁኔታ ምርታማ የመሬት አጠቃቀም በከፍተኛ ደረጃ ማሣደግ፤

   ለ)በዕቅድ ዝግጅት ወቅት ሕብረተሰቡን በሁሉም ደረጃዎች እንዲሣተፉ ማድረግ፤

   ሐ)የግብርናና የተፈጥሮ ኃብት ባለሙያዎችን ቴክኒካዊ እገዛ ማካተት ናቸው፡፡

## አንቀጽ 81

## የወረዳ አካባቢ አስተዳደር መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

የወረዳ የአካባቢ አስተዳደሮች የተሰጣቸውን ኃላፊነት ለማስፈፀምየሚያስችል መመሪያየማውጣት ሥልጣን አላቸው በዚህ መሠረት፡-

1. የአካባቢ አስተዳደሮች ለሚያስተዳድሩት አካባቢ በሙሉ ወይም በከፊል ተፈፃሚ የሚሆን ከፌዴራልና ከክልል ሕገ-መንግስት እንዲሁም የበላይ አስተዳደር እርከን ከሚያወጣው ህጐች ጋር በሚጣጣም መልኩ መመሪያ የማውጣት ሥልጣን አላቸው፡፡
2. መመሪያዎቹ ለማንኛውም ግለሰብ፣ ድርጅት፣ ተግባር ወይም ሌሎች ጉዳዮች ፈቃድ የመስጠትና ፈቃድ የመከልከል፣ የማገድ ወይም የመሰረዝ ሁኔታዎችን ሊደነግግ ይችላል፡፡
3. የአካባቢ አስተዳደር የአስተዳደሩ ምክር ቤት መመሪያውን ከማውጣቱ በፊት የሚመለከተውን ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴና ሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ክፍሎች ሃሳብና አስተያየት እንዲሰጡበት ያደርጋል፡፡
4. የአከባቢ አስተዳደር የአስተዳደሩ ምክር ቤት አስተያየቱን ከተቀበለ በኃላ ምክር ቤቱ መመሪያውን ያፀድቃል፡፡
5. ረቂቅ መመሪያው ከመጽደቁ በፊት ከሕገ-መንግስት ወይም ከሌላ ከማንኛውም ሕግ ጋር መጣጣሙን እንዲያረጋግጥ ለሚመለከተው የፍትህ ቢሮ ይልካል፤ በመጨረሻም መመሪያው እንዲፀድቅ ለአከባቢ አስተዳደር ምክር ቤት ያቀርባል፡፡
6. በማንኛውም መመሪያ ላይ ምክር ቤቱ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት፡-

   ሀ) የመመሪያ ቅጂ በምክር ቤቱ ጽህፈት ቤት ወይም ምክር ቤቱ ማስታወቂያ በሚያወጣበት ማንኛውም ቦታ ላይ ሆኖ ለማንኛውም ሰው እንዲታይ ለ14 ቀናት ግልጽ የማድረግ ወይም ተባዝቶ እንዲታወቅ ማድረግ አለበት፤

   ለ) ከላይ በንዑስ አንቀጽ 6 ወይም ሀ የተገለፀው መመሪያው ለአስተያየት ክፍት ከሆነበት የመጨረሻ ቀን ጀምሮ በ14 ቀናት ውስጥ በመመሪያ ላይ አስተያየት ወይም ተቋውሞ ያላቸው ሰዎች ተቃውሚቸውን በጽሁፍ ወይም በእንደራሴዎቻቸው በኩል እንዲያቀርቡ ይጋበዛሉ፡፡

7. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 6 በተገለፀው መሰረት በመመሪያው ላይ ተቃውሞ ከቀረበ ምክር ቤቱ ጉዳዩን እንደገና በማየት መመሪያውን እንደነበረ እንዲያልፍ ይወስናል ወይም በቀረበው ተቃውሞ መሠረት ያሻሽላል ወይም መመሪያውን ውድቅ ሊያደርግ ይችላል፡፡

8. የክልሉ ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ መመሪያው ከሕገ-መንግስቱ ወይም ከሌሎች ሕጎች ጋር የሚቃረን ሆኖ ካገኘው ተገቢው ማስተካከያ እንዲደረግበት በ90 ቀናት ውስጥ ወደ አካባቢ አስተዳደሩ ይመልሰዋል፡፡

## አንቀጽ 82

## መሬትንና ንብረትን ስለመያዝ

የወረዳ የአካባቢ አስተዳደሩ ቀጥሎ በተመለከተው ሁኔታ መሬትን የመያዝ ስልጣን ይኖረዋል፡-

1. ሕገ-መንግስቱና ሌሎች ማናቸውም ሕጎች እንደተጠበቁ ሁነው የአከባቢ አስተዳደር ማንኛውንም ተግባር ለማከናወን ወይም በዚህ አዋጅ የተሰጡትን ተግባራት ለማከናወን መሬቱ ለሕብረተ-ሰቡ ጤንነት አስፈላጊ መሆኑን በምክንያት ከደገፈ ወይም አካባቢውን ለማልማት ሲታቀድ የክልሉን መስተዳደር ምክር ቤት ዕውቅና በማግኘት በመሬቱ ላይያለውን ማንኛውንም መብት ግንባታ ያለውን ወይም የሌለውን መሬት በህግ መሠረት በግዴታ መውስድ ይችላል፤

2. ከግለሰቦች በግዴታ መሬት በሚወሰድበት ጊዜ ግለሰቦች በመሬቱ ላይ ላፈሰሱት ንብረት ወይም ሌላ ማሻሻያ ተመጣጣኝ ካሳ መከፈል አለበት፡፡ ዝርዝሩ በመሬት አጠቃቀምና አስተዳደር ህግ ይወሰናል፤

3. የአከባቢ አስተዳደር በከተማው መስፋፋት ምክንያት የተፈናቀሉትን ሰዎች የሚመለከተውን አካል በማማከር እንደገና እንዲሰፍሩ በማድረግ በዚህ ምክንያት ለሚያጡት ንብረት ተገቢውን ካሳ መክፈል አለበት፡፡

## አንቀጽ 83

## ግዥ

የወረዳ አካባቢ አስተዳደር ምክር ቤት በክልሉ የግዥ ሕግና ደንብ መሠረት አነስተኛ የቁሳቁስና የአገልግሎት ግዥ የሚመራበት ግልጽ የአገልግሎት ሥርዓት ይኖረዋል፤ሥርዓቱም፡-

1. ትክክለኛ፣ ግልጽና ተጠያቂነትን የሚያመለክት መሆኑ፤

2. በተለያየ ደረጃ ላይ የሚገኙ ኃላፊዎች እንዲያፀድቁ የሚፈቅድ መሆኑና፤

3. በአካባቢ አስተዳደሩ የሚወሰኑ ዋና ዋና ጨረታዎች ይፋ ማድረግን የሚያረጋግጥ መሆን አለበት፡፡

## ክፍል ሰባት

## የፋይናንስ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ 84

### የወረዳ አካባቢ አስተዳደር የፋይናንስ መርሆዎች

በክልሉ ውስጥ የአካባቢ አስተዳደር ፋይናንስ ቀጥሎ በተመለከቱት መርሆዎች ይመራል፡-

1. የአካባቢ አስተዳደር የፋይናንስ ምንጭ ከአካባቢው ከሚሰበሰበው ገቢና የክልል መንግስት ከሚሰጠው የበጀት ድጎማ ነው፤
2. የአካባቢ አስተዳደሮች የአካባቢያቸው የገቢ ምንጭ ላይ በቂ ግብር እንዲሰበሰቡ በማስቻል በራሳቸውና በሕዝቡ መካከል ውጤታማና ተጠያቂነት ያለበትን ግንኙነት መፍጠር አለባቸው፤
3. በክልሉ ውስጥ ከወረዳ አካባቢ አስተዳደሮች የሚላከው የበጀት ድጎማ ለአጠቃላይ አላማና ለተለየ ዓላማ የሚውል የበጀት ድጎማ ይሆናል፤
4. ከላይ በንዑስ የአንቀጽ 3 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ከክልሉ መንግስት የሚተላለፈው የበጀት ድጎማ ቅድሚያ ትኩረትበሚሰጡአቸው ሴክተር መስሪያ ቤቶችና በመደበኛና ካፒታል ወጪዎች መካከል ለይተው መደልደል እንዲችሉ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 93፣ 96 /3/መሠረት መተላለፍ አለበት፤
5. የክልሉ መንግስት በአፈፃፀም ላይ ያተኮረ የበጀት ቀመር ለአካባቢ አስተዳደር ተስማሚ ሆኖ ካገኘው የሚልከውን የበጀት ድጎማ በዚሁ መሠረት በሥራ ላይ ማዋል ይችላል፤
6. በዚህ ሕግና በሌሎች በፌዴራልና በክልል የግብር -ሕጐች ካልተደነገገ በስተቀር ማንኛውም የአካባቢ አስተዳደር የአገልግሎት ክፍያ፣ ወይንም ቀረጥ መሰብሰብ አይችልም፤ የአካባቢ አስተዳደሩ የተፈቀደለትን ግብር መሰብሰብና መጠቀም የሚችለው፡-

ሀ) በሕግ የሚፈለግባቸውን ኃላፊነት እንዲወጡ የሚያስተዳድሩትን አካባቢለማልማት በቁርጠኝነት እንዲነሳሱ፤

ለ) በአካባቢያቸው ያልተመጣጠነ እድገት ለማጥበብና፣

ሐ) ውጤታማና ብቃት ያለው የፋይናንስ አስተዳደር እንዲኖረውለማድረግ ነው፡፡

7. የአካባቢ አስተዳደሩ ያለፈውን፣ ያሁኑንና የወደፊቱን የፋይናንስ ተግባራትና መረጃዎች ለሕዝብ መስጠት አለበት፡፡

## አንቀጽ 85

## የክልል መንግስት ተግባር

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ እንደተጠበቀ ሆኖ የክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ በክልሉ ውስጥ የሚገኙ የአካባቢ አስተዳደሮች ፋይናንስ ይቆጣጠራል፣ ያስተዳድራል፤ የሚከተሉት ኃላፊነቶችም ይኖሩታል፡-

1. የአካባቢ አስተዳደሮችን የክልሉ የሰላም ግንባታና ፀጥታ ቢሮ የማማከር፤ ለአካባቢ አስተዳደሮች በጀት ዝግጅት የሚሆን ቅጽ፣ የጊዜ ሠሌዳና ዓመታዊ በጀት ለማዘጋጀት የሚረዳ መመሪያ ያወጣል፣

2. አግባብነት ያለውን አካል በማማከር እያንዳንዱ የአካባቢ አስተዳደር በበጀት ዓመቱ ለአጠቃላይና ለተለዩ ዓላማዎች የሚሰጣቸውን የበጀት ድጐማ መጠን ለመወሰን የሚያስችል ቀመር ያወጣል፣

3. ለአጠቃላይና ለተወሰኑ ተግባራት የሚመደብላቸው በጀት በሰኔ ወር የመጨረሻ ሳምንት ላይ ለአካባቢ አስተዳደሮች ማሣወቅ አለበት፣

4. የወጪ ማስረጃዎች ወይም ሌላ ሪፖርት በመቀበል ለአካባቢ አስተዳደሩ በየዓመቱ የበጀት ድጐማ መክፈል አለበት፣

5. ከክልሉ የሰላም ግንባታና ፀጥታ ቢሮበመተባበር የአካባቢ አስተዳደሩን ሪፖርት ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ ይገመግማልም፣

6. ለአካባቢ አስተዳደሮች የሚወጡ የፋይናንስና የሂሳብ ደንቦችን ያወርዳል፤ መመሪያዎች አዘጋጅቶ ያስተላልፋል፡፡

## አንቀጽ 86

## አማካሪ ኮሚቴ ቦርድ በክልል ለማቋቋም

የክልሉ መንግስት በአካባቢ አስተዳደር የፋይናንስ ጉዳይ ላይ የሚያማክር አንድ አካል ሊያቋቁም ይችላል፡፡ አማካሪ ቦርዱ ከ9 ያልበለጡ አባላት የሚኖሩት ሆኖ የክልል መንግስትና የአካባቢ አስተዳደሮች ተወካዮች የተውጣጣ ይሆናል፡፡ የክልሉ መንግስት በሚያዘጋጀው ደንብና መመሪያ መሠረት የቦርዱ አባላት ለ5 ዓመታት በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ይሰየማሉ፣

## አንቀጽ 87

## የፕላንና የፋይናንስ አማካሪ ቦርድ ተግባርና ኃላፊነት

የፕላንና የፋይናንስ አማካሪ ቦርድ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል፡-

1. ለአካባቢ አስተዳደሮች አጠቃላይና ውስን ተግባር የሚመደበውን በጀት በተመለከተ ያማክራል፤
2. የክልሉ መንግስት በአካባቢ አስተዳደሮች የተወሰነ ተግባር ለማስፈፀም ሲፈልግ የበጀት ድጐማ ስርዓቱንና በዲዛይን እንዲሁም አተገባበር ሂደት ክልሉን ያማክራል፤
3. በክልልና አካባቢ አስተዳደሩ መካከል በግብር አሰባሰብና ክፍፍል ላይ የክልሉን መንግስት ያማክራል፤
4. የአካባቢ አስተዳደሮች በየዓመቱ እንዲሰበስቡ ስለሚጠበቅባቸው የግብር መጠን ያማክራል፤
5. በክልሉ መንግስትና በአካባቢ አስተዳደሩ መካከል ያለመግባባት ሲፈጠር ሁለቱንም ወገኖች ያማክራል፤
6. በእቅድ ጉዳዮች ላይ ያማክራል፤
7. በክልሉ መንግስት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## አንቀጽ 88

## የወረዳ የአካባቢ አስተዳደር ገቢዎች

የወረዳ የአካባቢ አስተዳደር አግባብ ባለው የክልሉ የግብር ሕግ መሠረት ከሚከተሉት ምንጮች ግብር ይሰበስባል፡-

1. የወረዳው በጀት ደመወዝ ከሚከፈላቸው የመንግስት መ/ቤት ሠራተኞች ደመወዝ ገቢ ግብር፤
2. የወረደው አካባቢ አስተዳደሩ በሚያስተዳድራቸው የልማት ድርጅቶች ውስጥ ከሚሠሩ ሠራተኞች ደመወዝ ላይ የሚሰበስብ የገቢ ግብር፤
3. በወረዳ የአካባቢ አስተዳደር ውስጥ የሥራ ፈቃድ አግኝተው ከሚሠሩ ግለሰቦች ወይም ድርጅት ሠራተኞች ደመወዝ ላይ የሚሰበሰብ የገቢ ግብር፤
4. ከአርሶ አደሩ መሬት መጠቀሚያና ከእርሻ ስራ ገቢ ግብር፤
5. ከኪራይ ቤቶች እና ከግለሰብ የቤት ኪራይ ገቢ፤
6. ከንግድ ሥራ ገቢ ግብር፡-
   ሀ) በክልሉ ገቢ ግብር አዋጅ መሰረት ከደረጃ "ለ" እና "ከደረጃ ሐ" ነጋዴዎች፤
   ለ) ከአነስተኛ የማዕድን አምራች ድርጅቶች(አሸዋ፣ከድንጋይ አፈርእጣንና ሙጫ ንግድ ትርፍና ሮያሊቲ፤
   ሐ) በአካባቢ አስተዳደሩ ባለቤትነት ከሚተዳደሩ ድርጅቶች፤
7. ከግብርና ሥራ ውጭ ከሚገኙ ድርጅቶች የሚሰበሰብ የመሬት መጠቀሚያ ክፍያ ናቸው፡፡

<u>**አንቀጽ 89**</u>

<u>**የአገልግሎት ክፍያና ቀረጥ፤**</u>

የአካባቢ አስተዳደር በሚከተለው ሁኔታ የአገልግሎት ክፊያና ቀረጥ ሊሰበስብ ይችላል፡-

1. የአገልግሎት ክፍያ፡-
   ሀ) ከመንገዶች፣ ከድርጅቶች፣ ከመስኖ፣ ከውሃ ጉድጓዶችና ከጤና አገልግሎቶች፤
   ለ) በአካባቢ አስተዳደሩ ባለቤትነት ከሚተዳደሩ መኖሪያ ቤቶች፣ ቤት-መፃሕፍቶች፣ ክሊኒኮች፣ የስብሰባ አዳራሾች፣ ወዘተ፤
   ሐ) አካባቢን ለማልማት ከሚሰጡ ፍቃዶች፤
   መ) ከልደት፣ ከጋብቻ፣ ከፍቺ፣ ከሞትና ከውል ምዝገባዎች፤
   ሠ)በወረዳ ከሚሰበሰቡ ፍቃዶች፡፡

2. ቀረጦች፡-

ሀ) በግል ድርጅቶችና በአካባቢ አስተዳደሩ ባለቤትነት ከተያዙ ድርጅቶች የሽያጭ ታክስ፤

ለ) ከግልድርጅቶች የሚሰበሰብ ቀረጥ፤

ሐ) ከካፒታል ገቢ ታክስና፡፡

3. በሕግ እንዲሰበሰብ ከተፈቀደው ምንጭ የሮያሊቲ ክፍያን ይሰበስባል፡፡

## አንቀጽ 90

## ከሽያጭ የሚገኝ ገቢ

የወረዳ አካባቢ አስተዳደሩ ቀጥሎ ከተመለከቱት ገቢ ሊሰበስብ ይችላል፣

1. የሽያጭ ገቢ፡-

ሀ) ከሚንቀሳቀሱና ከማይንቀሳቀሱ የወረዳው አስተዳደር ንብረቶች፤

ለ) አሸዋ፣ ድንጋይ፣ አፈርና የግንባታ እንጨት፡፡

2. በአካባቢ ላይ አሉታዊ ሁኔታ በሚፈጠርበት ወቅትበሸቀጥነት የሚቀርቡየተፈጥሮ ሀብቶች ሽያጭ የተከለከለ ነው፡፡

3. በክልሉ መንግስት ከተከለከሉ ስፍራዎች ላይ የሚቀርቡ የተፈጥሮ ሀብትምርቶች በተለየ ሁኔታ ኃላፊነት ባለው አካል ፊቃድ ካልተሰጠው በስተቀር ለገበያ መቅረብ አይችልም፣

## አንቀጽ 91

## በወረዳ አስተዳደርና በክልሉ መንግስት መካከል ክፍፍል የሚደረግባቸው ገቢዎች፤

በወረዳ አስተዳደር የሚሰበሰቡ ገቢዎች በራሱና በክልሉ መንግስት መካከል በቀመር የሚከፋፈል ሆኖ ቀጥሎ ባለው ሁኔታ ይከፋፈላል፡-

1. ለግብርና ኢንቨስትመንት ሥራ በሊዝ ከተሰጠ መሬት እና የእርሻ ገቢ ግብር፤

2. ከትናንሽ ማዕድናት ማለትም ከድንጋይ፣አሸዋ፣አፈር፣እጣን፣ሙጫና ከፓታሽ ውጤቶች እና ከመሳሰሉት ከተፈጥሮ ሀብት ውጤቶች ውጪ ካሉት ማዕድኖች የሚሰበሰቡ የሮያሊቲ ክፍያዎችና የንግድ ትርፍ ገቢ ግብር፤

3. በወረዳ አስተዳደር ውስጥ የሚገኙ የቱሪዝም ስፍራዎችን ከሚጎበኙ ቱሪስቶች የሚሰበሰብ ክፍያ፤

4. የገቢ ክፍፍሉን በተመለከተ በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በሚወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

**አንቀጽ 92**

**የገቢ ክፍፍልን ስለማወጅ**

በአካባቢው አስተዳደሩ የተሰበሰቡ የገቢ መጠንና በአካባቢ አስተዳደርና በክልል መንግስት መካከል የተደረገው የገቢ ክፍፍል እንደ ዓመቱ በጀት አካል ሆኖ በወረዳ አካባቢ በአስተዳደር ይፀድቃል፡፡

**አንቀጽ 93**

**የክልል ድጎማ**

የአካባቢው አስተዳደር ከክልል መንግስት የሚያገኘው የድጎማ በጀት እንደሚከተለው ነው፡-

1. በአካባቢው አስተዳደር ለሚወሰን አጠቃላይ ድጎማ የሚውል በጀት፤
2. የክለሉ መንግስት በሚሰጠው መመሪያ መሠረት ለተወሰነ ዓላማ የሚውል የበጀት ድጎማ፤
3. የአካባቢው አስተዳደር የማስተካከያ፣ የማቻቻያ ወይም የማመጣጠኛ እና ከሥራ አፈፃፀም ጋር ተያይዞ የሚሰጥ ገንዘብ ሆኖ በማንኛውም ጊዜ በክልሉ መንግስት ሲወሰን ተቀብሎ የወረዳው የበጀት አካል አድርጐ ያፀድቃል፡፡

**አንቀጽ 94**

**ስለመበደርና ዋስትና**

የወረዳ አካባቢው አስተዳደር በክልሉ መንግስት ተወስኖ ስልጣንእስካልተሰጠው ድረስ ከማንኛውም ተቋም ወይም ግለሰብ ገንዘብ ሊበደር ወይም ዋስትና ለመስጠት አይችልም፡፡የብድር ሥርዓትና የመበደር ሥልጣን በክልል መስተዳድር ምክር ቤት በሚወጣው ደንብ ይወስናል፡፡

**አንቀጽ 95**

**የወረዳ አካባቢ አስተዳደር ገቢና ወጪ**

እያንዳንዱ የወረዳ አካባቢው አስተዳደር ገቢውንና ወጪውን የሚያስተዳድሩበትን አንድ ፈንድ ወይም ቋት ያቋቁማል፡፡ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤትም በሁሉም የወረዳ አካባቢው አስተዳደር ሊከተሉት የሚገባውን የፋይናንስና የተጠያቂነት ቁጥጥር በሚያሰፈን መልኩ የገንዘብ አያያዝና አጠቃቀም ደንብ ያወጣል፡፡ በተጨማሪም ፈንዱ በሚከተለው ሁኔታ ይተዳደራል፡-

1. ገንዘቡ ወይም ፈንዱ በባንክ ይቀመጣል፤
2. በወረዳ አካባቢው አስተዳደር የሚሰበሰብ ሁሉም ገቢ በፈንዱ ውስጥ ይቀመጣል፤
3. የወረዳው አካባቢው አስተዳደር የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ፈንዱን የማስተዳደር ኃላፊነት አለበት፤
4. በወረዳው አካባቢ አስተዳደር መ/ቤት አመታዊ በጀት ሆኖ ካልፀደቀ በስተቀር ከፈንዱ ወይም ቋቱ ወጪ አድርጐ መጠቀም አይቻልም፤
5. የፈንዱን አጠቃቀም የሚመለከት የፋይናንስ ሪፖርት በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት አማካይነት ቢያንስ በየሩብ ዓመቱ ለወረዳው አካባቢ አስተዳደር ምክር ቤት ለሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴና ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ሪፖርት ይቀርባል፤
6. በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ በሚወሰነው አነስተኛ የባንክ ሂሳብ ቁጥር መሠረት ፈንዱ የገቢና የወጪ የባንክ ሂሳብ ቁጥሮች ይኖሩታል፤
7. እያንዳንዱ የወረዳ አካባቢ አስተዳደር እንዳስፈላጊነቱ ተጨማሪ የባንክ ሂሳብ ቁጥሮች እንዲኖሩት ሊያደርግ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 96

## የወረዳ አካባቢ አስተዳደር በጀት

የወረዳ አካባቢ አስተዳደሮች በሚከተሉት ሁኔታዎች በጀታቸውን የማዘጋጀት፣ የማፅደቅና ስራ ላይ የማዋል ግዴታ አለባቸው፡-

1. የበጀቱ ገቢና ወጪ የተመጣጠነ መሆን አለበት፤
2. በጀቱ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ የተፈቀደ ፎርማት መከተል አለበት፤
3. በፌዴራልና ክልል መንግስት ቅድሚያ በሚሰጣቸው የሥራ መስኮች ላይ ቅድሚያ በመስጠት የበጀት ድልድል ማድረግ፤

4. በጀቱ በእያንዳንዱ ዓመት የሚሰበሰበውን ገቢና ሥራ ላይ የሚውለውን ወጪ ማሳየት አለበት፤
5. በጀቱ የዓመቱን የልማት ዕቅድ ግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት፤
6. በጀቱ በወረዳ አካባቢ አስተዳደር ከመጽደቁ በፊት እንደአግባብነቱ የአካባቢው ነዋሪ ጋር በትኩረት ጉዳዮች ዙሪያ ምክክር ሊደረግበት ይገባል፤
7. ግዴታውን ከመወጣት ተጨማሪ በጀቱ በግልጽ ካልተሰጠ ወይም ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ካልተፈጠረ በስተቀር በጀቱ ከተደለደለና ከፀደቀ በኋላ ተጨማሪ ገደብ አይጣልበትም፤
8. በጀት ከፀደቀ በኋላ እንደ አግባብነቱ የክልል መንግስት ወይም የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ደንብና መመሪያ መሠረት በጀትን ከአንዱ የበጀት ርዕስ ወደ ሌላው የበጀት ርዕስ ሊያዛውር ይችላል፡፡

**<u>አንቀጽ 97</u>**

**<u>የበጀት አመት</u>**

የወረዳ አካባቢ አስተዳደር የበጀት ዓመት በኢትዮጵያ አቆጣጠር ከሐምሌ 1 እስከ ሰኔ 30 ያለው ጊዜ ነው፡፡

**<u>አንቀጽ 98</u>**

**<u>የሂሣብ አያያዝ</u>**

እያንዳንዱ የአካባቢ አስተዳደር ተገቢ የሆነ የሂሳብ አያያዝና መዛግብት በሚከተለው መልክ የመያዝ ግዴታ አለበት፡-

1. ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ባወጣው መመሪያ የተመለከተውን አመዘጋገብ ፎርማት መከተል አለበት፣
2. ዝርዝር የፋይናንስ መግለጫ በየወሩ ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል መላክ አለበት፣
3. የሂሳብ መዝገቡ በወረዳው አካባቢ አስተዳደር ሥም የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽህፈት ቤት ይጠብቃል፣
4. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽህፈት ቤት የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የአመቱን የሂሳብ ሚዛንና መግለጫ ማቅረብ አለበት፡፡

**<u>አንቀጽ 99</u>**

## የወረዳ አካባቢ አስተዳደር ሂሳብ ምርመራ

እያንዳንዱ የወረዳ አካባቢ አስተዳደር ሂሣብ በሚከተለው መንገድ ይመረመራል፡-

1. የወረዳ አካባቢ አስተዳደር በየጊዜው በሚደረግ የገንዘብ አፈፃፀም ምርመራ የሴክተር መስሪያ ቤቶችን የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ማጠናከር አለበት፤
2. የወረዳ አካባቢ አስተዳደር ሂሳብ በየአመቱና እንደ አስፈላጊነቱ በክልላችን ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ወይም በክልሉ ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት መመርመር አለበት፤
3. የኦዲት ሪፖርቱ ለወረዳ አካባቢ አስተዳደር ምክር ቤት፣ሰላም ግንባታና ፀጥታ ቢሮ እና ለክልሉ መስተዳድርና ለዋናው ኦዲት መስሪያ ቤት ወይም ለክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ መላክ አለበት፤
4. ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤትም ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው የሂሳብ መዛግብትን፣ ሰነዶችንና ሌሎች ዶክመንቶችን በመመርመር ትክክለኛነታቸውን ሊያረጋግጥ ይችላል፤
5. የወረዳ አካባቢ አስተዳደር ምክር ቤት የኦዲት ሪፖርት ሲደርሰው አስተያየት እንዲቀርብ ወደ በጀትና ኦዲት ቋሚ ኮሚቴ ይመራል፤
6. ኮሚቴው ሪፖርት ለአጠቃላይ የምክር ቤት ጉባኤ ያቀርባል፤ ዋና አስተዳደሪውም የቀረበው የመፍትሄ ሐሳብ በተግባር ላይ መዋሉን ያረጋግጣል፤
7. የተዛባ የገንዘብ አጠቃቀም መኖሩ ሲደረስበት የሚመለከታቸው ግለሰቦች በዲሲፒሊን እና በህግ እንዲጠየቁ ይደረጋል፡፡

## አንቀጽ 100

## የወረዳ አካባቢ አስተዳደር ሐብትና ንብረት

የሁለቱም አካባቢው አስተዳደር ሀብታቸውን የሚመሩበትና የሚያስተዳድሩበትን ሥርዓት እንደሚከተለው መዘርጋት አለባቸው፡-

1. እያንዳንዱ ዋና አስተዳደር ሥራውን ሲጀምርና ሲያጠናቅቅ በያመቱየሚንቀሳቀሱና የማይቀሳቀሱ የአካባቢው አስተዳደር ንብረቶችን ቆጠራ እንዲደረግ ያደርጋል፣ ለአስተዳደር ምክር ቤቱና ለወረዳው ምክር ቤትም ሪፖርት ያቀርባል፤ሪፖርቱም፡-

   ሀ)ያለፈውን ዓመት የንብረት ዝርዝር፤

ለ) የንብረቱን አጠቃላይ ዋና ዋና ገጽታ፤

ሐ) ካለፈው ዓመት የዞረ፤

መ) የዋጋ ለውጥ፤

ሠ) የማይጠገኑ ዕቃዎች ዝርዝር፤

ረ)የጠፋ ንብረት ዝርዝር ካለ፤ ወይም

ሰ) በጥቅም ላይ ያሉ ዕድሳት ሊደረግላቸው የሚገቡና መወገድ ያለባቸውን ንብረቶች ያካተተ አስተያየት ማቅረብ አለበት፡፡

2. የአካባቢው አስተዳደር ንብረት ለሕዝብ ጥቅም ብቻ ይውላል፤

3. የሚንቀሳቀሱና የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች የሚወገዱት በክልሉ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ በሚያወጣው መመሪያመሠረት በማድረግ በወረዳ ምክር ቤት ውሳኔ ይሆናል፤

4. ማንኛውም የሚወገድ ንብረት በውድድርና በጨረታ ይሸጣል፤

5. በአካባቢው አስተዳደር ንብረት ከጠፋ ወይም ጉዳት ከደረሰበት ለአስተዳደር ምክር ቤቱ ሪፖርት መቅረብ አለበት፣ ተገቢ ሆኖ ሲገኝ ለጠፋው ወይም ለተጐዳው ንብረት ተጠያቂው ማን እንደሆነ ተለይቶ የጠፋው ንብረት ዋጋ ከሚመለከተው ሰው ወይም ሰዎች ተመላሽ መደረግ አለበት፣

## አንቀጽ 101

## ለቀበሌዎች የሚደረግ ድጋፍ

ቀበሌዎች የአካባቢው አስተዳደር ደረጃ የተወሰነ ሠራተኛ ብቻ ያላቸው በመሆኑ በጀት ሊኖራቸው ወይም ፈንድ ሊይዙ አይችሉም፡- ሆኖም

1. የተወሰነ ፕሮጀክት ወይም ፕሮግራም ለመፈፀም ከወረዳ ድጋፍ ሊሰጣቸው ይችላል፤ ይህም ሲሆን፡-

ሀ)ድጋፍ በወረዳው አስተዳደር ምክር ቤት መወሰን አለበት፤

ለ) ማንኛውም የሚሰጥ ድጋፍ ፕሮግራሙን ጠቀሜታ ያገናዘበ መሆን አለበት፤

ሐ) ዕርዳታው የሚወሰነው የተጠቃሚዎችን ቁጥር፣ የገንዘብ ችግር ደረጃንና የአካባቢውውን ተስማሚነት መሠረት በማድረግ ነው፤

መ) የተሰጠው ዕርዳታ በተግባር የሚውለው በግልፀኝነትና በተጠያቂነት መሆን አለበት፡፡

## ክፍል ስምንት

## የአካባቢው አስተዳደሮች የእርስ በርስና ከክልሉ መንግስት ጋር ያለው ግንኙነት፣

### አንቀጽ 102

### የአካባቢው አስተዳደር ክትትልና ቁጥጥር

1. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የአካባቢው አስተዳደሮችን የመደገፍና የመቆጣጠር ኃላፊነት የክልሉ የሰላም ግንባታና ፀጥታ ቢሮ ማከናወኑን ያረጋግጣል፤

2. ይህን አዋጅ በሁሉም የአካባቢው አስተዳደሮች ተፈፃሚ ለማድረግ የሚያስችሉ ሥልጣንና ተግባራት ለክልሉ የሰላም ግንባታና ፀጥታቢሮ በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል፡፡

3. የክልሉ የሰላም ግንባታና ፀጥታ ቢሮ የአካባቢው አስተዳደሮች ግዴታቸውንና ስልጣናቸውን በሕገ-ወጥ ወይንም ብቃት በሌለው ሁኔታ እየተወጡ መሆናቸውን ካረጋገጠ የአካባቢው አስተዳደሩ ጋር ስብሰባ በማድረግ የታዩትን ሕገ-ወጥ አሰራሮች በመግለጽ ማስተካከያ ይሰጣል፣

4. የክልሉየሰላም ግንባታና ፀጥታ ቢሮ በአካባቢ አስተዳደሩ የተፈፀሙ የአሰራር ችግሮች ከባድና ከአቅም በላይ መሆናቸውን ከተገነዘበ የቢሮ ኃላፊው ተገቢው የሆነ አጣሪ አካል እንዲቋቋም ለክልሉ መስተዳድር ኃሳብ ሊያቀርብ ይችላል፣

5. የአጣሪ ኮሚቴው ጥፋት መፈፀሙን በምርመራው ካረጋገጠ ተገቢው ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን ከተገቢው የውሳኔ አስተያየት ጋር ወደክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ያስተላልፋል፣

6. የክልሉየሰላም ግንባታና ፀጥታቢሮ በአካባቢው አስተዳደሮች መካከል ወይም በውስጣቸው የሚነሱ አለመግባባቶችን በማስማማት ይፈታል፡፡

## አንቀጽ 103

## የማገድና የማፍረስ ሥልጣን

1. የክልሉ ምክር ቤት በቂ ምክንያት በማቅረብ በሕገ-መንግስቱ ድንጋጌ መሠረትየአካባቢውን አስተዳደር በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ማገድ የሚችለው፡-

   ሀ) የአካባቢው አስተዳደር ሲጠይቅና የሕዝቡ ጥቅም መሆኑ ሲረጋገጥ፤ ወይም

   ለ) በአካባቢው አስተዳደር የተፈፀመው ተግባር ብሔራዊ ሉአላዊነትን፣ ብሔራዊ ወይም ክልላዊ ጥቅምንና ሕገ-መንግስታዊውን ስርዓት አደጋ ላይ የሚጥል መሆኑ ሲታመን ወይም፤

   ሐ) የአካባቢው አስተዳደር የመንግስት ገቢን ለግል ጥቅም ወይም በሌላየሙስና ተግባር ላይ መሰማራቱ ሲታመን ወይም፤

   መ) የአካባቢው አስተዳደር ያለ በቂ ምክንያት ከአንድ ዓመት በላይያልተሰበሰበ ከሆነ ወይም፤

   ሠ) የአካባቢው አስተዳደር የአስተዳደር ምክር ቤት ያለ በቂ ምክንያት ከ6 ወር በላይ ያልተሰበሰበ ከሆነ ናቸው፤

2. አስገዳጅ ሁኔታ ካልቀረበ በስተቀር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተጠቀሰው እገዳ ተግባራዊ ከመሆኑ አስቀድሞ የአካባቢው አስተዳደር የእገዳውን ምክንያት ተቃውሞ በጽሑፍ የማቅረብና የመደመጥ እድል ይሰጠዋል፣

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የአካባቢው አስተዳደር ከታገደ የአካባቢውን አስተዳደር የተለመደ ተግባሩን ለማከናወን እንዲችል የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት አስፈላጊውንና ጊዜያዊውን አደረጃጀት ይፈጥራል፣

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተጠቀሰው እገዳ ሥራ ላይ ከዋለ የክልሉ መንግስት በ3 ወር ጊዜ ውስጥ ጉደዩን የሚያጣራ ኮሚቴ ያቋቁማል፣

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ምርመራ ተካሂዶ የአካባቢ አስተዳደሩን ማፍረስ የሚያበቃ በቂ ምክንያት ከተገኘ የክልል ምክር ቤት የአካባቢው አስተዳደሩ እንዲፈርስ ሊወስን ይችላል፣

6. በዚህ አንቀጽ መሠረት የአካባቢው አስተዳደር ከፈረሰ በወረዳው የተፈጥሮ አደጋ፣ የኢኮኖሚ አለመረጋጋት ወይም ይህንን ለመፈፀም የሚያስቸግር ሌላ ምክንያት ካላጋጠመ በስተቀር በምርጫ ቦርድ እውቅና በ6 ወራት ጊዜ ውስጥ የማሟያ ምርጫ መደረግ አለበት፡፡ እንደ ችግሩ ስፋት ታይቶ የማሟያ ምርጫ የሚደረግበት ጊዜ ለአንድ ዓመት ሊራዘም ይችላል፣

7. አዲስ የአካባቢ አስተዳደር እስከ ሚመረጥና አስተዳደር ምክር ቤት እስከ ሚሰየም ድረስ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የአካባቢውን አስተዳደር ይመራል፡፡

## አንቀጽ 104

## የክልሉ መንግስት ለአካባቢ አስተዳደር ስለሚሰጠው ድጋፍ

1. የሰላም ግንባታና ፀጥታ ቢሮ የአካባቢ አስተዳደሩን አቅምና ብቃት የማሳደግ ግዴታ አለበት፤ ይህንን በሚያደርግበት ጊዜ የሚከተሉትን ሁኔታዎችን ማረጋገጥ አለበት፡-

   ሀ) የክልል ቢሮዎች የወረዳ ሴክተር መስሪያ ቤቶቻቸው በየሩብ ዓመቱበሚያቀርቡት የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ላይ ግብረ መልስ የመስጠት ግዴታ አለባቸው፤

   ለ)የወረዳ አከባቢ አስተዳደርም ሆነ ሴክተር መሥሪያ ቤቶች ስትራቴጂያዊ ዕቅድና ዓመታዊ ዕቅድ በሚያዘጋጁበት ጊዜ አገራዊና ክልላዊ ራዕይ ፖሊሲና ስትራቴጂ ከወረዳው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ ለማዘጋጀት የክልል ቢሮዎች ሁለንተናዊ ድጋፍ የመስጠት ግዴታ መወጣታቸውን ማረጋገጥ፣

   ሐ) በወረዳ አካባቢ አስተዳደር የሚሰሩ ዋና ዋና የልማትና የመልካም አስተዳደር ሥራዎችን የክልል ኃላፊዎች ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ በአካል እንዲጎበኙ በማስተባበርና በማስተግበር፤

   መ) በወረዳዎች መካከል ያለውን ያልተመጣጠነ የማስፈፀም ብቃት ማንበብ የሚመለከታቸውን የክልል መሥሪያ ቤቶችን በማስተባበር የቴክኒክና ሙያ እንዲሁም የልማት ሥራዎችን የሚያግዝ የእገዛ ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ በማድረግ፤

ሠ) ከሚመለከታቸው ከሌሎች ሴክተር ቢሮዎች ጋር በመሆን የአካባቢ አስተዳደርንና ሴክተር ጽህፈት ቤቶቻቸውን ለመከታተልና ለመገምገም የክትትልና የግምገማ ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

2. የክልሉ ሴክተር መሥሪያ ቤቶች በሙያቸው ዙሪያ የአከባቢ አስተዳደሩ ሴክተር ጽህፈት ቤቶች ቴክኒካዊና ቁሳዊ ድጋፍ የመስጠትና አቅማቸውን የመገንባት ግዴታ አለባቸው፣ ይህንንም፡-

   ሀ) የእያንዳንዱ የቢሮ ባለሞያዎች ቢያንስ በየ6 ወሩ ወደ ወረዳ ሴክተር መስሪያ ቤቶቻቸው በመውረድ ሙያዊና ቴክኒካዊ ድጋፍ የመስጠት ግዴታ፤

   ለ) የክልል መሥሪያ ቤቶች ለወረዳዎች የሚሰጧቸውን ቁሳዊ ድጋፍ መንግስታዊ ከሆኑና ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመቀናጀት መደገፍ አለባቸው፤

3. የሰላም ግንባታና ፀጥታ ቢሮ የአካባቢ አስተደደር የሚመለከቱ ጉዳዮችን የማስተባበር ሥልጣን ያለው ሲሆን፡-

   ሀ) የአካባቢውን አስተዳደር የሚመለከቱ አጠቃላይ ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ መወሰን አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ የመንግስትን ተወካዮችና ሌሎች ሴክተር ቢሮዎች ባንድ ላይ ለመጥራትና ለመወያየት የሚያግዝ ተገቢ የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት፤

   ለ) በጋራ ጉዳዮች ላይ የሚመክር የአካባቢ አስተዳደሮች መደበኛ ስብሰባ ያዘጋጃሉ፤

   ሐ) የአካባቢ አስተዳደሮች የልማትና የመልካም አስተዳደር ትብብር የመሠረቱ ከሆነ አስፈላጊ በሆኑ አስተዳደር ጉዳዮች ላይ እንዲሳተፍ ትኩረት ይሰጣል፡፡

## አንቀጽ 105

## የመተባበር ግዴታ

1. የአካባቢ አስተዳደሮች ሥራውን በአካባቢያቸው ከሚገኙ ማናቸውም ከተሞች ወይም የከተማ አስተዳደር ጋር በቅንጅት መሥራት አለባቸው፤ ስለዚህ የጋራ ኮሚቴ ሊያቋቁሙ ይችላሉ፡፡
2. የክልሉ ሴክተር ቢሮዎች በወረዳ አካባቢ አስተዳደሮች የልማት ሥራዎች ላይ የተለያዩ ድጋፎችን ሲጠየቁ የመደገፍ ግዴታ አለባቸው፡፡
3. የወረዳ አካባቢ አስተዳደሮች ለክልሉ ልማት ሥራ አስፈላጊ መረጃዎችን እንዲሰጡ በክልሉ ባለሥልጣናትና በሌሎች ሲጠየቁ ተገቢውን መረጃ በመስጠት የመተግበር ግዴታ አለባቸው፣

## አንቀጽ 106

## በወረዳ አካባቢ አስተዳደሮች መካከል ስለሚኖረው ግንኙነት

1. በክልሉ ውስጥ ያሉ የወረዳ አካባቢ አስተዳደሮች የጋራ ፍላጐታቸውን የሚወክል ማህበር ሊያቋቁሙ ይችላሉ፡፡
2. ማህበሩ መመዝገብና በህጉ መሰረት ተግባሩን ማከናወን አለበት፤ የክልሉ መንግስትም ለዚህ ማህበር እውቅና የመስጠትና አብሮ የመሥራት ግዴታ አለበት፡፡
3. የማህበሩ መዋቅርና የአሠራር ሁኔታ በመመስረቻ ጽሁፎቹ ላይ ይወሰናል፡፡
4. አዋሣኝ የአካባቢ አስተዳደሮች የጋራ ጥቅም ባላቸው ጉዳዮች ላይ አብሮ ለመተግበርና ለመሥራት እንዲሁም የጋራኮሚቴዎችን በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ለማቋቋም ይችላሉ፡፡
5. በአካባቢ አስተዳደሮች መካከል ግጭቶች ሲነሱ በአካባቢው ደረጃ እልባት አንዲያገኙ የተቻለውን ሁሉ ጥረት ያደርጋል፤ ተገቢው ጥረት ተደርጎ ለአስተዳደርና የፀጥታ ጉዳዮች ማስተባበሪያ ቢሮ በመግለጽ ወይም በአስማሚ እንዲፈታ ይደረጋል፡፡

## አንቀጽ 107

## በወረዳና በቀበሌዎች መካከል ስለሚኖረው ግንኙነት

1. የወረዳ አካባቢ አስተደደሮች ቀበሌዎች ለሚፈጽሟቸው ሥራዎች ድጋፍ፣ ምክርና መረጃ የመስጠት ግዴታ አለባቸው፣
2. የወረዳ አካባቢ አስተዳደሮች በቀበሌዎች መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን በአስማሚ ወይም በአስተዳደራዊ ሁኔታ ይፈታሉ፣

## ክፍል ዘጠኝ

## የሰው ኃይል

### አንቀጽ 108

### የሠራተኞች ድልድልና መዋቅር

1. የአካባቢ አስተደደሮች የመስሪያ ቤታቸውን ተገቢውን መዋቅር በመሥራት ለክልሉ መንግስት ለተጨማሪ ትችትና ስምምነትበሚልኩበት ወቅት የሚከተሉትን ነገሮች ታሳቢ ማድረግ አለባቸው፡-

    ሀ)የአደረጃጀት ለውጡን፤

    ለ)የሚሰጡትን አገልግሎቶች፤

    ሐ) የመዋቅሩን ወጪ፤

    መ) የገንዘብ አቅማቸውንና ገቢያቸውን፤

    ሠ)የታቀደውን የሥራ ክብደት፤

    ረ)የሰለጠነ የሰው ኃይል በአካባቢያቸው መገኙቱን፤

    ሰ)በክልሉ ቢሮዎች የተሰጣቸውን አቅጣጫዎች ናቸው፡፡

2. ከክልሉ መንግስት ጋር በተደረገው ስምምነት መሠረት የአካባቢ አስተዳደሩ የአስተዳደር ምክር ቤት ያዘጋጀውን መዋቅር ለአካባቢ አስተዳደሩ ምክር ቤት በማቅረብ ያፀድቃል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ አንድ የተቀመጠው ቢኖርም የአካባቢ አስተዳደር መስሪያ ቤት ወይም መስሪያ ቤቶች ሊቋቋሙ፣ ሊሰፉ፣ ሊጠቡ ወይም ጨርሰው ሊፈርሱ ይችላሉ፡፡

### አንቀጽ 109

### የሠራተኞች ምደባ

የወረዳ አካባቢ አስተዳደር በሚከተለው መሰረት የሰው ኃይል የማስተዳደር ሥልጣንና ሃላፊነት ይኖሩታል፡-

1. የወረዳ አካባቢ አስተዳደሩ በፀደቀው የሠራተኞች መዋቅር መሠረት ሠራተኞችን ይቀጥራል፤
2. በክፍት የሥራ መደቦች ማስታወቂያ በማውጣት በቦታው የሥራ ብቃት ልምድ ያላቸውን ባለሙያዎች ይቀጥራል፤
3. እያንዳንዱ የአካባቢ አስተዳደር ሠራተኛ በሚሰራበት የመሥሪያ ቤት ኃላፊ በኩል ለአካባቢ አስተዳደሩ ተጠሪ የሥራ አፈፃፀማቸውን ሥራን ማዕከል ባደረገ መልኩ መዘርዝራቸውና ተወስኖ በሚሰጣቸው ሥራ ተመዝኖ በአመት ሁለት ጊዜ ይሞላል፤
4. ማንኛውም የወረዳ አካባቢ አስተዳደር ሴክተር ጽህፈት ቤት ለአስቸኳይና ለጊዜያዊ ሥራ በአጭር ጊዜ ውል ጊዜያዊ ሠራተኞችን ሊቀጥር ይችላል፤
5. የአካባቢ አስተዳደር በውል ስምምነትና በዚህ አዋጅ የግዥ አንቀጽ መሠረት ለተወሰነ ቆይታ ኮንትራክተር ወይም አማካሪ ሊቀጥር ይችላል፤ በዚህ ጊዜ የሚመለከተውን የክልል ቢሮ ወይም ሴክተር ጽ/ቤት በቅጥር ሂደት ላይ ምክር ይጠይቃል፤
6. የአካባቢ አስተዳደር በራሱ ጥረት ብቻ ሊያሟላ የማይችለውን የሠራተኞች ክፍተት ለመሙላት ለተወሰነ ጊዜ የባለሙያ ትብብር ከክልሉ መንግስት ሊጠይቅ ይችላል፤
7. የሚመለከተው የክልሉ ሴክተር ቢሮ ወይም የክልሉ መንግስት ባለሙያ ትውስት ጥያቄ ከተቀበለ ሠራተኛው ለሚሰራቸው ሥራዎች ለአካባቢ አስተዳደሩ ተጠሪ ሲሆን ለሌሎች ጉዳዮች በሙሉ ደግሞ ለክልሉ መንግስት ወይም ለሚመለከተው የክልሉ ሴክተር ቢሮ ይሆናል፤
8. የአካባቢ አስተዳደር የሰው ኃይል አስተዳደር ሁኔታ በክልሉ የመንግስት ሰራተኛ ደንብና መመሪያ መሠረት ይወሰናል፡፡

### <u>አንቀጽ 110</u>

### <u>የሠራተኞች ክፍያና የሥራ ሁኔታዎች</u>

1. ክፍያ፣ የክፍያ ጊዜና የሠራተኛው የአገልግሎት ሁኔታ በክልሉ የመንግስት ሰራተኛ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ መሠረት ይሆናል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ አንድ ቢኖርም የአካባቢ አስተዳደር የክልልን መንግሥት በማማከር የገንዘብ አቅማቸውን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ለሠራተኞቻቸውና ለተሿሚዎቻቸው በጥናት ላይ የተመሠረተ የተለያዩ አበልና ጥቅማ-ጥቅም እንዲወሰንላቸው ለክልሉ መስተዳደር ምክር ቤት ጥያቄ ሊያቀርቡ ይችላሉ፡፡
3. የወረዳ አካባቢ አስተዳደር ከክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ጋር በመመካከርና ከክልሉ መንግሥት የሚሰጠውን አቅጣጫ መሠረት በማድረግ እንዲሁም የገንዘባቸውን አቅም ከግንዛቤ በማስገባት በአስቸጋሪ አካባቢ ለሚሰሩ ሠራተኞችና ተሿሚዎችየአስቸጋሪ አካባቢ የበረሃ አበልና ሌሎችን ጥቅማ-ጥቅሞች ሊወስኑ ይችላሉ፡፡

## አንቀጽ 111

## የሥነ-ምግባር ደንብ

1. የክልሉ የመንግሰት ሠራተኞች በክልሉ የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ኮሚሽን በሚያወጣውና ወይም በድጋፋቸው እያንዳንዱ ቢሮ በሚያዘጋጀው የሥነ-ምግባር ደንብ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፣
2. ሁሉም የሲቪል ሠርቪስ ሠራተኞች ለሚፈጽሙት የዲሲፕሊን ጥፋት በክልሉ የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ የዲሲፕሊን አፈፃፀም ሥነ-ምግባር ደንብና መመሪያ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፣
3. በሌሎች ህጐች የተደነገገውና ከፍ ብሎ በንዑስ አንቀጽ አንድ የተጠቀሰው ቢኖርም ማንኛውም ኃላፊ ወይም ሠራተኛ ከዚህ በታች ለተጠቀሱት በሙስናና በሌሎች ህጐች መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡-

ሀ)የአካባቢውን አስተዳደር ንብረት ወይም ገንዘብ በመመዝበር፤

ለ) አካባቢ አስተዳደሩ ከሚከፍለው ውጪበማጭበርበር፣በማታለል፣ በማስገደድ ወይም በሽልማት መልክ ወይም በሌላ አይነት ምንም አይነት ክፍያ እንዲሰጠው ሊጠይቅ አይችልም፤

ሐ)የአካባቢውን አስተዳደር ወክሎ በሚያደርገው ድርድር ወይም በሚገባው ውል የገንዘብ ጥቅም ወይም በጉዳዩ ላይ የራሱ የተለየ ጥቅም ወይም ውል ከሚገባባቸው ወገኖች ጋር ምንም አይነት አግባብ የሌለው ግንኙነት የሌለው መሆኑ መረጋገጥ አለበት፡፡

## አንቀጽ 112

## የሥልጠናና የሰው ኃይል ልማት

1. እያንዳንዱ የአካባቢ አስተዳደር ሴክተር ጽህፈት ቤት የሠራተኞችን ሥልጠና የመለየት፣ ሥልጠናዎችን የማዘጋጀት፣የሥልጠናና የሰው ኃይል ልማት በጀት የመመደብ፣ ሥልጠና የመስጠትና የመስሪያ ቤቱ የሥራ አፈፃፀም በቅልጥፍና፣ በግልጽነትና በተጠያቂነት ላይ የተመሠረተ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡
2. የክልሉ ሴክተር ቢሮዎች የአካባቢ አስተዳደሮችን አቅም መገንባት ኃላፊነት ያለባቸው ሲሆን ከአካባቢው አስተዳደሮች ጋር በቅርብ በመሥራት የኘሮግራሞችን አፈፃፀም በቅንጅትና በተሳካ ሁኔታ ማረጋገጥ አለባቸው፣
3. የክልሉ የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ኮሚሽን የአካባቢ አስተዳደሮችን አጠቃላይ የሰው ኃይል ልማት ችግሮችን የመለየትና የሌሎች አካላትን ጥረት ማስተባበር መፍትሄ የመስጠት ኃላፊነት አለበት፣

## ክፍል አስር

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## አንቀጽ 113

## ደንቦችና መመሪያዎችን የማውጣት ሥልጣን

በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት አካላት ደንቦችንና መመሪያዎችን የማውጣት ሥልጣን አላቸው፣

1. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ይህን አዋጅ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ደንቦችንና መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፣
2. የሚመለከተው ቢሮና የአካባቢ የሰላም ግንባታና ፀጥታ ቢሮ በሕግ ከተሰጣቸው ሥልጣንና ተግባር አንፃር በዚህ አዋጅመሠረት የሚወጡ ደንቦችን ለመተግበር የሚረዱ መመሪያዎችን ማውጣት ይችላሉ፣

3. የወረዳ አካባቢ አስተዳደሮች በክልሉ ሕገ-መንግስት ከተሰጠው ስልጣን በተጨማሪ ከላይ በንዑስ ቁጥር 1 እና 2 በተጠቀሱት አካላት ከሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች ጋር የተጣጣሙና ኃላፊነታቸውን በብቃት ለመወጣት የሚያስችሉ ዝርዝር መመሪያዎችን ሊያወጡ ይችላሉ፡፡

## አንቀጽ 114

## ስለ ብሄረሰብ አስተዳደር

የብሄረሰብ የአካባቢ አስተዳደር ከክልልም ሆነ ከሌሎች የአከባቢ አስተዳደሮች ጋር ስለሚኖረው ግንኙነትም ሆነ ስለራሱ የሥልጣን ሁኔታ የብሄረሰብ የአካባቢ አስተዳደሩ ተግባራዊ ሲደረግ በመስተዳድር ምክር ቤቱ በሚወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

## አንቀጽ 115

## ሀብቶችን፣መብቶችንና ግዴታዎችን ስለማስተላለፍ

1. ቀደም ሲል በወጡ ሕጐችና በተፈፀሙ ድርጊቶች የተገኙ የወረዳ የአካባቢ አስተዳደሮች ሀብቶችና ዕዳዎች እንዲሁምመብቶችና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ መሠረት ለሚተኩአቸው ወይም አዲስ ለሚቋቋሙ አካባቢ አስተዳደሮች ይተላለፋሉ፣
2. ቀደም ሲል የነበሩ የአካባቢ አስተዳደሮች በነባሩ ሕጎች አማካይነት የፈፀሟቸው ተግባራትና የወሰዷቸው እርምጃዎች በዚህ አዋጅ መሠረት በሚተኳቸው ወይም በሚቋቋሙ የአካባቢ አስተዳደሮች እንደተፈፀሙ ተግባራትና እንደተወሰዱ እርምጃምች ይቆጠራሉ፣

## አንቀጽ 116

## የተሻሩናተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጐች

1. የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት ያልተማከለ የአካባቢ አስተዳደርን ለማጠናከር የወጣ አዋጅ ቁጥር 86/2002 ዓ/ም ተሽሯል፣
2. የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት ያልተማከለ የአካባቢ አስተዳደርን ለማጠናከር የወጣ አዋጅ 86/2002 ዓ/ምን ለማረም የወጣ አዋጅ ቁጥር 104/2004 ዓ/ም ተሽሯል፣

3. የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት ያልተማከለ የአካባቢ አስተዳደርን ለማጠናከር የወጣ አዋጅ ቁጥር 86/2002 ዓ/ም በከፊል ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 144/2009 ዓ/ም በዚህ አዋጅ ተሽሯል፤

4. ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም አዋጅ ወይም ልማዳዊ አሠራር ይህ አዋጅ በሸፈናቸው ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፣

**አንቀጽ 117**

**አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ የክልሉ ምክር ቤት ካፀደቀበት ጊዜ ጀምሮ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

አሶሳ

-------ቀን 2012 ዓ/ም

አሻደሊ ሀሰን አልአጀብ

የቤኒሻጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት

ፕሬዝዳንት